Amerigroup
District of Columbia







## Amerigroup District of Columbia, Inc. Alliance

# የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ

DHCF Department of Health Care Finance

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is brought to you by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.

1046354DCMAMAGP 12/24

Do you need help with your health care, talking with us, or reading what we send you? We provide our materials in other languages and formats at no cost. Call us toll-free at 1-800-600-4441 (TTY 711). English

¿Necesita ayuda con el cuidado de la salud, para hablar con nosotros o para leer lo que le enviamos? Le ofrecemos nuestros materiales en otros idiomas y formatos sin costo alguno. Llame a nuestra línea gratuita al 1-800-600-4441 (TTY 711). Spanish

በእርስዎ የጤና ክብካቤ ላይ፣ ከእኛ ጋር በመነጋገር ላይ፣ ወይም እኛ የምንልክልዎትን ነገሮች በማንበብ ላይ እገዛ ያስፈልግዎታል? የእኛን የሚነበቡ ነገሮች በሌሎች ቋንቋዎች እና ቅርጸቶች በእርስዎ ላይ ምንም ወጪ ሳያስከትልብዎት እንሰጥዎታለን። በነጻ የስልክ መሥመር በስልክ ቍጥር1-800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉልን። Amharic

건강 관리에 도움이 필요하십니까? 아니면 저희와 연락하시거나, 보내드리는 자료를 읽는데 도움이 필요하십니까? 자료를 다른 언어 및 형식으로 무료로 제공해드립니다. 저희에게 1-800-600-4441 (TTY 711) 번으로 연락해 주십시오. Korean

您在醫療保健方面、與我們交流或閱讀我們寄送的材料時是否需要幫助？我們可為您免費提供其他語言和格式的材料。請撥打我們的免費電話 1-800-600-4441（聽障專線 711）。 Chinese Traditional

Avez-vous besoin d’aide pour vos soins de santé, pour parler avec nous ou pour lire ce que nous vous avons envoyé ? Nous pouvons vous fournir gratuitement nos documents dans d’autres langues et formats. Appelez notre numéro gratuit 1-800-600-4441 (TTY 711). French

Quý vị có cần trợ giúp liên quan tới chăm sóc sức khỏe, nói chuyện với chúng tôi, hoặc đọc nội dung chúng tôi gửi cho quý vị không? Chúng tôi có cung cấp tài liệu bằng các ngôn ngữ và định dạng khác mà không tính phí cho quý vị. Hãy gọi chúng tôi theo số điện thoại miễn cước 1-800-600-4441 (TTY 711). Vietnamese

N̂ a jlȧ bò mamȧɛ̇ kȯ n̂-ȧ fuɛjı̇-ȧ jȧ ėti nlɔnlɔɛ-ȧ tèh bò, mɔ̀ɔ̇ bê yė-lė âmô bò wlu, mɔ̀ɔ̇ bê yė dɛ nė â a mua mû bò dlo slɛ̀? Dɛ wɛ̀ nė â a clėa, â a po-lė i dakɔ̇+ tê-ȧ win klı̇ kà nė i a mua i-ȧ nyati wɔnwɔ̇ɛ̀n nu, ɛ se pɛnȯ kpȯh ne. Dȧ âmô, ɛ se pɛnȯ kpȯh ne 1-800-600-4441 (TTY 711). Kru

ヘルスケアの受診、ご相談時の会話、配布物の読解にお困りではありませんか？当院では無料の翻訳版資料をご用意しております。無料ダイアル 1-800-600-4441 (TTY 711) までお電話ください。 Japanese

Вам нужна помощь в получении медицинских услуг, вы хотите поговорить с нами или не можете прочитать присланные вам материалы? Наши материалы можно бесплатно получить на других языках и в другом формате. Позвоните нам по бесплатному номеру 1-800-600-4441 (TTY 711). Russian

Necessita de ajuda com a sua assistência médica, para falar connosco, ou para ler o que lhe enviamos? Fornecemos os nossos materiais noutros idiomas e noutros formatos, sem qualquer custo para si. Ligue-nos gratuitamente para 1-800-600-4441 (TTY 711). Portuguese

Ha bisogno di aiuto con la sua assistenza sanitaria, per parlare con noi o per leggere ciò che le abbiamo inviato? I nostri materiali sono disponibili in altre lingue e formati senza alcun costo per lei. Può contattarci gratuitamente al numero 1-800-600-4441 (TTY 711). Italian

Kailangan ba ninyo ng tulong sa inyong pangangalagang pangkalusugan, sa pakikipag-usap sa amin, o sa pagbabasa ng aming ipinadadala sa inyo? Ipinagkakaloob namin ang aming mga materyal sa iba pang mga wika at format na wala kayong babayaran. Tawagan kami nang toll free sa 1-800-600-4441 (TTY 711). Tagalog

คุณต้องการความช่วยเหลือในด้านการดูแลสุขภาพของคุณ พูดคุยกับเรา หรืออ่านสิ่งที่เราจัดส่งให้คุณหรือไม่ เราจัดส่งสื่อของเราเป็นภาษาและรูปแบบอื่นๆ โดยไม่มีค่าใช้จ่าย โทรหาเราฟรีที่ 1-800-600-4441 (TTY 711) Thai

Ị chọrọ enyemaka na nlekọta ahụike gị, ịgwa anyị okwu, ma ọ bụ ịgụ ihe anyị zitere gị? Anyị na enye ihe anyị n’asụsụ na nhazi ndị ọzọ na akwụghị ụgwọ ọ bụla. Kpọọ anyị n’efu na 1-800-600-4441 (TTY 711). Igbo

Njẹ́ o nílò ìrànlọ́wọ́ nípa ìtọ́jú ìlera rẹ, ní bíbá wa sọ̀rọ̀, àbí kíkà ohun tí a fi ránṣẹ́ sí ọ? A npèsè àwọn nnkan wa ní àwọn èdè míràn àti ní irú míràn fún ọ láì díyelé. Pè wá lọ́fẹ̀ẹ́ ní 1-800-600-4441 (TTY 711). Yoruba

আপনার কি আপনার স্বাস্থ্য পরিচর্যা, আমাদের সঙ্গে কথা বলার ক্ষেত্রে অথবা আমরা আপনাকে যা পাঠায় তা পড়তে সহায়তার প্রয়োজন? আমরা অন্য ভাষা ও ফর্ম্যাটে বিনামূল্যে আমাদের সামগ্রী প্রদান করি। আমাদের টোল-ফ্রি নম্বর 1-800-600-4441 (TTY 711) এ ফোন করুন। Bengali

Benötigen Sie Hilfe bezüglich Ihrer Gesundheitsversorgung, möchten Sie mit uns sprechen oder haben Sie Probleme, die von uns zugesandten Materialien zu verstehen? Wir stellen Ihnen unsere Materialien auch in anderen Sprachen und Formaten kostenfrei zur Verfügung. Sie erreichen uns gebührenfrei unter 1-800-600-4441 (TTY 711). German

**ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች**

<table>
<tr><td rowspan="2">ስለ እርስዎ የ የሚተዳደር የእንክብካቤ እቅድ (MCP) ጥያቄዎች ካሉዎት</td><td>የተመዝጋቢ አገልግሎቶች</td><td>800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td>TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች</td><td>711 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የሐኪምዎ ቢሮ ከተዘጋ በኋላ ህክምና ካስፈለገዎት፥</td><td>የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine)</td><td>800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td>TTY/TDD የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine)</td><td>711 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td rowspan="2">በ24 ሰዓታት ውስጥ ሐኪም ማየት የሚያስፈልግዎት ከሆነ (“አስቸኳይ ሕክምና”)፡-</td><td><u>የእርስዎ ዋና የሕክምና አቅራቢ (PCP)</u> ቢሮ</td><td colspan="2">(የእርስዎን የ <u>PCP</u> መረጃ እዚህ ይሙሉ)</td></tr>
<tr><td>የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine)</td><td>800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td>ወደ ቀጠሮ ለመሄድ ትራንስፖርት ካስፈለገዎት፥</td><td>የተመዝጋቢ አገልግሎቶች</td><td colspan="2">Medical Transportation Management (MTM)<br>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት<br>888-828-1081 (TTY 711) (ከክፍያ ነፃ)</td></tr>
<tr><td rowspan="2">የባህሪ ጤና እንክብካቤ ከፈለጉ ወይም ጥያቄ ካለዎት፥</td><td>የእርስዎ <u>የእርስዎ የባህሪ ጤና (BH)</u> ቢሮ</td><td colspan="2">የDC የባህርይ ጤና ተደራሽነት መምሪያ የስልክ መስመር ላይ በ1-888-793-4357፣ 24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት።</td></tr>
<tr><td>የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse HelpLine)</td><td>800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ቋንቋዎን መናገር የሚችል ሰው ከፈለጉ ወይም መስማት የተሳነዎት ከሆኑ፥</td><td>የተመዝጋቢ አገልግሎቶች</td><td>800-600-4441 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>TTY/TDD የተመዝጋቢ አገልግሎቶች</td><td>711 (ከክፍያ ነፃ)</td><td>ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>የጥርስ ህክምና ጥያቄዎች፥</td><td>Avesis</td><td>833-554-1012</td><td>ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 ሰዓት</td></tr>
<tr><td>የዓይን ህክምና ጥያቄዎች፥</td><td>Avesis</td><td>833-554-1012</td><td>ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 ሰዓት</td></tr>
<tr><td colspan="4">ለድንገተኛ ሁኔታ፣ ወደ911 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኘው የድንገተኛ ክፍል ይሂዱ</td></tr>
</table>

**የግል መረጃ**

**የእኔ የአሊያንስ ID፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP)፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) አድራሻ፥**

---

**የኔ ዋና ሕክምና አቅራቢ (PCP) ስልክ፥**

---

**የእኔ ተቀዳሚ የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) ስም፥**

---

**የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP) አድራሻ፥**

---

**የኔ ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ (PDP)፥**

---

**የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ ስም፥**

---

**የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ አድራሻ፥**

---

**የእኔ የባህርይ ጤና አቅራቢ ስልክ፥**

---

**ማውጫ**

**ጠቃሚ የስልክ ቁጥሮች ... 4**

**እንኳን ወደ Amerigroup DC በደህና መጡ ... 9**

ስለዚህMCP ... 9

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል ... 9

**መብቶችዎ ... 10**

**ግዴታዎችዎ ... 10**

**የእርስዎ የተመዝጋቢID ካርድ ... 12**

**የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP) ... 13**

PCP ምንድን ነው? ... 13

የእርስዎንPCP እንዴት መምረጥ ይችላሉ? ... 13

የእርስዎንPCP እንዴት መቀየር ይችላሉ? ... 13

**የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP) ... 14**

PDP ምንድን ነው? ... 14

የእርስዎንPDP እንዴት መምረጥ ይችላሉ? ... 14

የእርስዎንPDP እንዴት መቀየር ይችላሉ? ... 14

**መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና ... 14**

መደበኛ ህክምና ... 15

አስቸኳይ ህክምና ... 15

የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና ... 15

**ከከተማ ውጭ ሲሆኑ ህክምና ... 15**

**ከአውታረ-መረብ ውስጥ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች ... 16**

**ቀጠሮ ማስያዝ ... 16**

የእርስዎPCP ወይምPDP ... 16

ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ ... 17

የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት ... 17

ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? ... 17

**የድጋፍ አገልግሎቶች ........ 18**
የትራንስፖርት አገልግሎቶች ........ 18
እንግሊዝኛ ቋንቋን በደንብ መናገር የማይችሉ ከሆነ የሚሰጡ አገልግሎቶች ........ 18
የመስማት ወይም የማየት ችግር ካለብዎት የሚሰጡ አገልግሎቶች ........ 19
**የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራል ........ 19**
የስፔሺያሊቲ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ........ 19
የራስ-የሪፈራል አገልግሎቶች ........ 19
የባህሪይ ጤና አገልግሎቶች ........ 20
የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ........ 21
መድሃኒቶችን እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ........ 22
በሽታ መቆጣጠር ........ 23
የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች ........ 23
**አዋቂ ሰዎችን ከመታመም የሚከላከሉ አገልግሎቶች ........ 24**
የክትትል ምርመራዎች ምክረሀሳቦች (“ማጣሪያዎች”) ........ 24
የመከላከል የምክር አገልግሎት ........ 24
የአዋቂ ክትባቶች ........ 24
**እርግዝና - ልጅ መውለድ ........ 24**
የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ ሕክምና ........ 25
**የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች ........ 25**
በAmerigroup DC የሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶች ........ 25
ክፍያቸውን የማንሸፍነው አገልግሎቶች ........ 28
**ሌላ ጠቃሚ መረጃ ........ 28**
ቦታ ከቀየርኩ ምን ማድረግ ይኖርብኛል ........ 28
ህጻን ልጅ ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ ........ 28
ህጻን ልጅ በማደጎ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ ........ 28
ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ ........ 28
የእኔን MCP እንዴት መቀየር እንደምችል ........ 29
ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ሲደርስዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ ........ 29
ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ክፍያ መፈጸም ........ 29
የቀደመ መመሪያ ........ 30

ለሐኪምዎ እንዴት እንደምንከፍል ላይ ልዩ መረጃ ........ 30
ማጭበርበር ........ 30

**ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ........ 30**
ቅሬታዎች ........ 30
ይግባኞች ........ 31
ፍትሃዊ ችሎቶች ........ 31
የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት ........ 32
በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሎት መብቶች ........ 32

**የግላዊነት ልምድ ማስታወቂያ ........ 32**

**የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ ........ 36**

**ትርጉሞች ........ 38**

**እንኳን ወደ Amerigroup DC በደህና መጡ**

Amerigroup District of Columbia, Inc.ን እንደ የጤና እቅድዎ ስለመረጡ እናመሰግናለን። እኛ የDC Healthcare Alliance ፕሮግራም ተመዝጋቢዎችን በማገልገላችን ኩራት ይሰማናል።

ይህ የተመዝጋቢ መመሪያ መጽሐፍ ስለ Amerigroup DC እና የጤና እቅድዎ እንዴት እንደሚሰራ ጠቃሚ መረጃ አለው። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት። እንደ Amerigroup DC ተመዝጋቢ እንደ መከላከያ ምርመራዎች፣ ምርመራዎች፣ መድሃኒቶች፣ እና የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ የመሳሰሉ መደበኛ የጤና ጥቅማጥቅሞች እና ጤናማ ኑሮ እንዲኖሩ እና ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎ የሚያግዙ ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞች አሎት።

በየወሩ፣ አዲስ የተመዝጋቢ ገለጻ (ኦሪየንቴሽን) እናዘጋጃለን። ይህ ስለ Amerigroup DC ጥቅማጥቅሞችዎ የበለጠ የሚማሩበት ሌላ መንገድ ነው። በገለጻው ወቅት፣ ለጥያቄዎችዎ መልስ ለማግኘት ከቡድናችን አባል ጋር በተጨማሪ መነጋገር ይችላሉ። ከእኛ ጋር አሁኑኑ መነጋገር ይፈልጋሉ? እኛ አንድ መጫን ወይም ስልክ መደወል ብቻ ርቀን እንገኛለን። ወደ መለያዎ (አካውንትዎ) ይግቡ ወይም በመስመር ላይ (ኦንላይን) ይመዝገቡ፣ በ **myamerigroup.com/DC**። ደህንነቱ የተጠበቀ የጽሁፍ መልእክት ይላኩልን ወይም የስልክ ቀጠሮ ያስይዙ። ወይም ለእኛ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ቡድን በ800-600-4441 (TTY 711) ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት8፡00 እስከ ምሽት6፡00 ይደውሉ። በእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ልንረዳዎት እዚህ እንገኛለን።

**ይህ የመምሪያ መጽሃፍ እንዴት እንደሚሰራ**

በጤና ህክምና እና በሐኪም የሚገለጹ ቃላት አንዳንድ ጊዜ ለመረዳት አስቸጋሪ ናቸው። Amerigroup DC የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ ማግኘት እንዲችሉ ለማገዝ በColumbia ዲስትሪክት ክፍያ የሚከፈል ቁጥጥር የሚደረግበት የህክምና እቅድ ነው። በዚህ የመምሪያ መጽሃፍ Amerigroup DC እንዴት እንደሚሰራ፣ ሐኪሞችን እንዴት እንደሚያገኙ፣ ወደኛ እንዴት መደወል እንደሚችሉ፣ እና እኛ ስለምንከፍላቸው ነገሮች ይነግርዎታል። በትርጉሞች ክፍል፣ የእነዚህን ቃላት ፍቺ በዚህ መጽሃፍ ጀርባ ላይ አብራርተናል።

በዚህ መጽሃፍ ስላነበቡት ነገሮች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ወይም ስለ Amerigroup DC ሌሎች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ለAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) መደወል ወይም **myamerigroup.com/DC** መጎብኘት ይችላሉ፣ እና እኛ እርስዎን ለማገዝ የተቻለንን እናደርጋለን።

**ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሀፍ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል**

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ የሚከተሉትን ይነግርዎታል፥

- የጤና እንክብካቤን እንዴት እንደሚያገኙ
- የእርስዎ የተሸፈኑ አገልግሎቶች በAmerigroup DC
- በAmerigroup DC የማይሸፈኑ አገልግሎቶች
- ዋና የህክምና አቅራቢዎን እና ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢዎን (የእርስዎPCP ወይምPDP) እንዴት መምረጥ እንደሚቻል
- ሲታመሙ ምን ማድረግ እንዳለብዎ

**ቅሬታ ካለዎት ወይም Amerigroup DC የሰጠውን ውሳኔ ማስለወጥ (ይግባኝ ማለት) ከፈለጉ ምን ማድረግ እንዳለብዎት**

ይህ የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ Amerigroup DC እንደሚሰራ መሰረታዊ መረጃ ይሰጥዎታል። ማንኛውም ጥያቄዎች ካሎት እባክዎ ወደ Amerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በማንኛውም ጊዜ፣ 24 ሰዓት በቀን እና 7 ቀናት በሳምንት ይደውሉ።

**መብቶችዎ**

- ከሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች ጋር ሲያወሩ፣ ሚስጥራዊ መሆኑን ማወቅ
- በሚረዱት ቋንቋ በሽታው ወይም ሕክምናው እንዲገለጽልዎ መደረግ
- ስለ ሕክምናዎ በሚደረጉ ውሳኔዎች መሳተፍ፣ ሕክምና ያለመቀበል መብትን ጨምሮ
- በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲያደርጉ የተሟላ፣ ግልጽ እና ለመረዳት የሚቻል የሕክምና አማራጮችን እና የእያንዳንዱን አማራጭ አደጋ ማብራሪያ ማግኘት
- እንክብካቤ ወይም ሕክምና ማግኘት አለመፍቀድ
- ለማስገደድ፣ ለዲስፒሊን፣ ለምቾት፣ ወይም ለበቀል ዓላማ ከሚደረጉ ማንኛውም ገደቦች ወይም የመገለል ሁኔታዎች ነጻ መሆን
- የሕክምና ሪከርዶችዎን ማየት እና ቅጂ ማግኘት እንዲሁም ስህተት ካለበት እንዲሻሻል ወይም እንዲቀየር የመጠየቅ
- ያሉትን እና ለእርስዎ ተደራሽ የሆኑትን የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን በተገቢው ጊዜ ማግኘት
- ብቁ የሆነPCP/PDP ከAmerigroup DC መረብ (ኔትዎርክ) ውስጥ መምረጥ እና የእርስዎንPCP/PDP መቀየር
- ስላገኙት ሕክምና ቅሬታ ማቅረብ እና ምላሽ ማግኘት
- Amerigroup DC አገልግሎት ወይም እቃ በመከልከል፣ በመቀነስ ወይም በማቋረጥ ትክክል አይደለም ብለው ካመኑ፣ ይግባኝ ወይም ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ
- ከሚመርጡት አቅራቢ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶችን ማግኘት
- ያለ አላስፈላጊ መዘግየት የሕክምና እንክብካቤ ማግኘት
- በመረቡ ውስጥ ካለ፣ ወይም አስፈላጊ ከሆነ፣ ከመረብ ውጭ ከሆነ፣ ብቁ ከሆነ የጤና ሕክምና ባለሞያ፣ እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ፣ ሁለተኛ አስተያየት ማግኘት
- የቀደመ መመሪያዎች ላይ መረጃ ማግኘት እና ማንኛውም የህይወት ማቆያ ሕክምናን ያለማግኘት ወይም ማግኘት መቀጠልን መምረጥ
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ የመምሪያ መጽሃፍ እና የአቅራቢ ማውጫ ቅጂን ማግኘት
- አዲስ የሕክምና እቅድ እስኪያገኙ ድረስ አሁን እያገኙ ያለውን ሕክምና ማግኘት መቀጠል
- የቃል ትርጉም እና የትርጉም አገልግሎቶችን ያለ ምንም ወጪ መቀበል
- የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን ማግኘትን አለመቀበል
- ያለ ምንም ወጪ የትራንስፖርት አገልግሎት መቀበል
- የቀደመ ፈቃድ ሂደቶች ላይ ማብራሪያ ማግኘት
- ስለ የAmerigroup DC የገንዘብ ሁኔታ እና ለሐኪሞቻችን ክፍያ ስለምንፈጽምበት ማንኛውም ልዩ ዘዴዎች መረጃ ማግኘት
- የደምበኛ እርካታ የዳሰሳ ጥናቶች ማጠቃለያዎችን ማግኘት
- በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶችን በተመለከተ የAmerigroup DC "በተጻፈው መሰረት ይጠቀሙ" የሚል ፖሊሲ ማግኘት
- ሽፋን ያላቸውን የሁሉንም መድሃኒቶች ዝርዝር ማግኘት
- ሰብዓዊነትዎን እና የግል ነጻነት መብትዎን ባከበረ መልኩ በክብር መታየት

**ግዴታዎችዎ**

የሚከተሉት ግዴታዎች አሉብዎት፥

- ህክምና የሚሰጥዎትን ሰዎች በአክብሮት እና በክብር መያዝ
- የDC Medicaid የተቀናጀ የሕክምና ፕሮግራም እና የAmerigroup DC ህጎችን ማክበር
- ሐኪሞችዎ እና ሌሎች አቅራቢዎች የሚሰጥዎትን መመሪያዎች መተግበር
- በተያዙት ቀጠሮዎች መገኘት
- ቀጠሮውን መሰረዝ ካለብዎ ቢያንስ ከ 24 ሰዓታት በፊት ለሐኪምዎ መንገር


- የሐኪምዎ ትእዛዝ ካልገባዎ ተጨማሪ ማብራሪያ መጠየቅ
- ድንገተኛ ሕክምና ሲያፈልግዎ ብቻ ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ
- ጤናዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለ ሚችሉ የሕክምና እና የግል ችግሮች ለእርስዎPCP/PDP መንገር
- እርስዎ ወይም የቤተሰብ ተመዝጋቢ ሌላ የጤና መድን ካላችሁ ወይም የአድራሻ ወይም የስልክ ቁጥር ለውጥ ካለ፣ ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) እና Amerigroup DC ሪፖርት ማድረግ
- በቤተሰብዎ ውስጥ ማንኛውም ለውጥ ካለ (ማለትም፥ ሞት፣ ልደት፣ ወዘተ) ለESA እና Amerigroup DC ሪፖርት ማድረግ
- የጤና ችግሮችዎን ለመረዳት መሞከር እና የሕክምና ግቦች ዝግጅት ላይ መሳተፍ
- ሐኪምዎ ከዚህ በፊት እርስዎን ካከሙ አቅራቢዎች የሕክምና ሪከርዶችዎን እንዲያገኙ ማገዝ
- በአደጋ ምክንያት ወይም ሥራ ላይ ከተጎዱ ለAmerigroup DC ማሳወቅ

<u>**የእርስዎ የተመዝጋቢ ID ካርድ**</u>


ዋና የሕክምና አቅራቢ (PCP) አንድ ጊዜ ከተመደበልዎ በኋላ፣ የተመዝጋቢ ID ካርድ በፖስታ እንልክልዎታለን። ይህ ካርድ የእርስዎ ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች፣ የመድሃኒት መደብሮች፣ እና ሌሎች እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን እንዲያውቁ ያስችላቸዋል። እባክዎ በተመዝጋቢ ID ካርድዎ ላይ ያለው መረጃ ትክክል መሆኑን ያረጋግጡ። ማንኛውም ችግሮች ካሉ፣ ወይም ካርድዎ ከጠፋብዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። እያንዳንዱ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ የራሳቸው ካርድ አላቸው። የተመዝጋቢ ID ካርድዎን ማንኛውም ሰው እንዲጠቀምበት ማድረግ በህግ የተከለከለ ነው።

**የተመዝጋቢ ID ካርድዎ ይህን ይመስላል፥**

**የካርዱ ፊትለፊት**




**የካርዱ ጀርባ**




እባክዎ የተመዝጋቢ ID ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለበት መታወቂያ ሁልጊዜ መያዝ ያስታውሱ። ማንኛውም የህክምና እንክብካቤ ከማግኘትዎ በፊት ወይም ከመድሃኒት ቤት መድሃኒት ከመውሰድዎ በፊት ሁልጊዜ ካርድዎን ያሳዩ።

## <u>የእርስዎ ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)</u>

እርስዎ አሁን የAmerigroup DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎPCP (ዋና የሕክምና አቅራቢ) እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎPCP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup DC ከመመደብዎ በፊት PCP ከነበሮት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)። ከፈለጉ ከዚያPCP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

### የእርስዎንPCP መምረጥ

1. እርስዎ Amerigroup DC ጋር ሲመዘገቡPCP ይምረጡ። ይህ ሰው የAmerigroup DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎPCP ይሆናሉ።
   - የእርስዎ የአሁንPCP የAmerigroup DC መረብ(ኔትዎርክ) አቅራቢ ከሆኑ፣ እዚያ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
   - እርስዎPCP ከሌለዎት፣ ከኛ የአቅራቢ ማውጫ ካለው ዝርዝር ወይም **myamerigroup.com/DC** ጋር መምረጥ ይችላሉ።
   - ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለገዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
   - በAmerigroup DC ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥPCP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትንPCP ካልወደዷቸው፣ የእርስዎንPCP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎንPCP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
   - Amerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ የእርስዎን የPCP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።
2. በAmerigroup DC ውስጥ ላሉት ለእያንዳንዱ የቤተሰብ ተመዝጋቢPCP ይምረጡ። የእርስዎPCP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
   - የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሙሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
   - የውስጥ ደዌ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ አዋቂ እና እድሜያቸው 14 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ልጆችን ብቻ ያክማሉ።
   - አዋላጅ ሐኪም/የማህጸን ሐኪም (OB/GYN) - የሴቶች ጤና እና የወሊድ ሕክምና ላይ ያተኮረ ነው።
   - እርስዎ ልዩ የጤና ሕክምና የሚያስፈልጎት ከሆነ፣ ስፔሺያሊስትን እንደ PCP መምረጥ ይችላሉ።
3. የእርስዎንPCP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተሉትን ያድርጉ፥
   - ለቤትዎ ወይም ለሥራዎ አቅራቢያ የሆነ ሐኪም ይምረጡ።
   - ሁሉም ሐኪሞች ታካሚዎችን ወደ ሁሉም ሆስፒታሎች መላክ አይችሉም። ወደሚፈልጉት ሆስፒታል ሊልክዎ የሚችሉ ሐኪም ይምረጡ።
   - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡትPCP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድPCP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
   - ሌላ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

### የእርስዎንPCP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ

የእርስዎንPCP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። አዲስPCP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስPCP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስPCP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## <u>የእርስዎ ዋና የጥርስ ህክምና አቅራቢ (PDP)</u>

እርስዎ አሁን የAmerigroup DC ተመዝጋቢ በመሆንዎ፣ የእርስዎPDP (ዋና የጥርስ ሕክምና አቅራቢ) እርስዎ እና ቤተሰብዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና እንክብካቤ እንድታገኙ ይረዳዎታል።

ሕክምና ሲያስፈልግዎ መጀመሪያ የእርስዎPDP ጋር መደወል አስፈላጊ ነው። ወደ Amerigroup DC ከመመደብዎ በፊት የጥርስ ሀኪም ከነበረዎት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ከፈለጉ ከዚያ PDP ጋር እንዲቆዩ ልንረዳዎ እንችላለን።

### የእርስዎንPDP መምረጥ

1. እርስዎ Amerigroup DC ጋር ሲመዘገቡPDP ይምረጡ። ይህ ሰው የAmerigroup DC ተመዝጋቢ ሆነው በሚቆዩበት ጊዜ የእርስዎPDP ይሆናሉ።
    - የእርስዎ የአሁንPDP የAmerigroup DC አውታረ-መረብ አቅራቢ ከሆኑ፣ ከዚያ የጥርስ ሐኪም ጋር መቆየት ይችላሉ።
    - እርስዎPDP ከሌለዎት፣ በአቅራቢ ማውጫችን ውስጥ ካለው የጥርስ ሐኪሞች ዝርዝር ወይም በ **myamerigroup.com/DC** መምረጥ ይችላሉ።
    - የጥርስ ሐኪም ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለገዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
    - በAmerigroup DC ውስጥ በተካተቱ በመጀመሪያዎቹ 10 ቀናት ውስጥPDP ካልመረጡ፣ እኛ ለእርስዎ የጥርስ ሐኪም እንመርጥልዎታለን። እኛ የመረጥንልዎትንPDP ካልወደዱቸው፣ የእርስዎንPDP መቀየር ይችላሉ። የእርስዎንPDP ለመቀየር የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
    - Amerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይልክልዎታል። ካርድዎ ላይ የእርስዎን የPDP ስም እና የስልክ ቁጥር ይኖረዋል።
2. በእኛ እቅድ ውስጥ ያሉ የእያንዳንዱን ተመዝጋቢ ቤተሰብPDP ይምረጡ። የእርስዎPDP ከሚከተሉት አንዱ ሊሆኑ ይችላሉ፥
    - የቤተሰብ እና አጠቃላይ የጥርስ ሐኪም - አብዛኛውን ጊዜ ቤተሰቡን ሁሉ ሊያክሙ ይችላሉ።
3. የእርስዎንPDP ሲመርጡ፣ እባክዎ የሚከተለውን ያስተውሉ፥
    - የኛ የአቅራቢ ማውጫ አንድPDP እርስዎን ወደየትኞቹ ሆስፒታል ሊልክዎ እንደሚችል ይዘረዝራል። በተጨማሪ ለእርዳታ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ።
    - አንዳንድ ጊዜ፣ የሚመርጡትPDP አዲስ ታካሚዎችን መቀበል አይችልም። ሌላ የጥርስ ሐኪም መመረጥ የሚኖርብዎ ከሆነ እናሳውቅዎታለን።

### የእርስዎንPDP እንዴት መቀየር እንደሚችሉ

የእርስዎንPDP በማንኛውም ጊዜ መቀየር ይችላሉ። ከአቅራቢ ማውጫ አዲስPDP መመረጥ ብቻ ነው። አዲስPDP ለመምረጥ እርዳታ ካስፈለጎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ሊያግዝዎ ይችላሉ። አዲስPDP ከመረጡ በኋላ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## <u>መደበኛ ህክምና፣ አስቸኳይ ህክምና፣ እና ድንገተኛ ህክምና</u>

ሶስት (3) አይነት የጤና እንክብካቤ ሊያስፈልግዎ ይችላል፥ መደበኛ፣ አስቸኳይ ወይም ድንገተኛ።

**መደበኛ ህክምና**

መደበኛ ሕክምና ማለት ከእርስዎPCP የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና ማለት ነው። መደበኛ ሕክምና የእርስዎPCP ከላክዎት ሌሎች ሐኪሞች የሚያገኙት ሕክምናንም ይጨምራል። መደበኛ ሕክምና የክትትል ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ምርመራ፣ እና የስኳር፣ የደምግፊት፣ እና አስም የመሳሰሉ የጤና ችግሮች ሕክምና ሊሆን። መደበኛ ሕክምና ካስፈለጎት፣ የእርስዎ የPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ቀጠሮ ለመያዝ ይጠይቁ።

**አስቸኳይ ህክምና**

አስቸኳይ ሕክምና ማለት ወዲያውኑ ሳይሆን በ 24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። አንዳንድ አስቸኳይ የሕክምና ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው፥

- ማስታወክ
- ራስ ምታት
- ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን ከመጠን በላይ መጠቀም
- አነስተኛ ቃጠሎ ወይም ጥቃቅን ቁስል
- የጉሮሮ ህመም
- የባህሪይ ጤና
- የጆሮ ህመም
- የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር
- ከ 101 ዲግሪ ፋራናይት በላይ ትኩሳት

**አስቸኳይ ሕክምና የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ የእርስዎ የPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ።** የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የስልክ ጥሪ የሚቀበለው ሰው ጋር መልእክት ያስቀምጡ። ከዚያ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ የስልክ መስመር (24-hour Nurse Help Line) ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ይነግርዎታል። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

**የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና**

ድንገተኛ ሕክምና ማለት ለከባድ እና ድንገተኛ (አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ የሆነ) ጉዳት ወይም በሽታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ የሕክምና እንክብካቤ ማለት ነው። ለድንገተኛ ሕክምና ማንኛውንም ሆስፒታል የመጠቀም መብት አሎት። ለድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች ቅድመ ፈቃድ አያስፈልግም።

- የመተንፈስ ችግር
- የደረት ሕመም
- ራስን መሳት
- የማይቆም በጣም ከባድ የደም መፍሰስ
- በጣም ከባድ ቃጠሎ
- ኮንቮልዥን ወይም ሲዠር ተብሎ የሚጠራ መንቀጥቀጥ
- እየተባባሰ የሚሄድህ ህመም

**ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥምዎ ምን ማድረግ እንደሚችሉ**

1. **ወደ 9-1-1 ይደውሉ ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል (ER) ይሂዱ**
2. **የእርስዎን የAmerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ያሳዩ**
3. **በተቻልዎ ፍጥነት፣ የእርስዎPCP ጋር ይደውሉ።**

**ከከተማ ውጭ ሲሆኑ ህክምና**

ከከተማ ውጭ ሆነው በሐኪም መታየት ወይም መድሃኒት መውሰድ ካስፈለጎት፣

**መደበኛ ህክምና**

ከከተማ ውጪ ሐኪም ጋር ወይም ሌላ አቅራቢ ጋር ሲሄዱ ለሐኪም የምንከፍልልዎ መሆን አለመሆኑን ወደኛ ደውለው መጠየቅ አለብዎት ምክንያቱም በColumbia ዲስትሪክት ውስጥ ያልሆኑ ሐኪሞች የAmerigroup DC አካል አይደሉም። ሕክምናውን ከማግኘትዎ በፊት Amerigroup DC እንደሚቻል ካልነገሮት፣ የሚከፍሉት እርስዎ እራስዎ ኖት። ከከተማ ውጭ ሆነው ከሐኪም መድሃኒት ካስፈለግዎ፣ የእርስዎPCP ጋር ይደውሉ። እርዳታ ከፈለጉ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር ጋር (24-hour Nurse Help Line) በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**አስቸኳይ ህክምና**

ወደPCPዎ መደወል አለብዎ። የእርስዎ PCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ የስልክ መስመር (24-hour Nurse Help Line) ላይ በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ነርሱ/ሷ ሐኪም ጋር ወዲያውኑ መሄድ ያለብዎ መሆን አለመሆኑን እንዲወስኑ ያግዝዎታል። ነርሱ/ሷ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንዳለብዎ ሊነግርዎ ይችላሉ። ለመደበኛ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ወደ ድንገተኛ ሕክምና ክፍል (ER) መሄድ ወይም አምቡላንስ መጠቀም አያስፈልግዎትም።

**የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና**

የባህሪይ ጤና፣ የአልኮል፣ ወይም ሌላ የአደንዛዥ እጽ ድንገተኛ አደጋን ጨምሮ ድንገተኛ አደጋ ካጋጠመዎት፣ አቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ህክምና ክፍል (ER) በአፋጣኝ ህክምና ለማግኘት ይሂዱ። ወደER ከገቡ፣ የER ሰራተኞች ወደ እርስዎ PCP እንዲደውሉ መጠየቅ አለብዎት። ወደER ከገቡ፣ በተቻለ ፍጥነት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይኖርብዎታል። **ለድንገተኛ ሕክምና አገልግሎቶች ቅድመ ፈቃድ አያስፈልግም።**

**ከአውታረ-መረብ ውስጥ እና ከአውታረ-መረብ ውጭ ያሉ አቅራቢዎች**

Amerigroup DC ወደ አንዱ ሐኪማችን ወይም ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ጋር ሲሄዱ ለእርስዎ ሕክምና ይከፍላል። እኛ እነዚህን ሐኪሞች እና ሌሎች የጤና ሕክምና አቅራቢዎች የእኛ “መረብ” አቅራቢዎች ብለን እንጠራቸዋለን። የእኛ ያልሆነ ሐኪም ወይም አቅራቢ “ከመረብ ውጪ” አቅራቢ ተብሎ ይጠራል። እነዚህ ሁሉም “የመረብ ውስጥ” ሐኪሞች በአቅራቢ ማውጫዎ ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ።

“ከመረብ ውጪ” የሆነ ሐኪም፣ ሆስፒታል፣ ወይም ላብራቶሪ ጋር ከሄዱ፣ ለሕክምናዎ መክፈል ሊኖርብዎት ይችላል። መጀመሪያ እኛን ቢጠይቁን እና እኛ እንደሚቻል፣ አብዛኛውን ጊዜ በጽሁፍ፣ ነግሮኖት ቢሆን ኖሮ፣ መክፈል አይኖርብዎትም ነበር። እኛ ይህን “የቀደመ ፈቃድ” ብለን እንጠራዋለን።

**የቀደመ ፈቃድ (PA)** ማለት በመደበኛነት በAmerigroup DC ሽፋን ላልተሰጠው የጤና አገልግሎት ፈቃድ ማለት ነው። አገልግሎቱን ከማግኘትዎ በፊት ይህን ፈቃድ ማግኘት አለብዎ። ድንገተኛ ሕክምና ለማግኘትPA አያስፈልግዎትም።PA ስለ ማግኘት ለመጠየቅ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

ከመረብ ውጪ ቢሆኑም፣ የመረጡት የቤተሰብ ምጣኔ አቅራቢ ጋር መሄድ ይችላሉ። የቀደመ ፈቃድ አያስፈልግም። ገጽ 21 ይመልከቱ፣ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን የሚመለከቱ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት።

በመረብ ውስጥ ያለ አቅራቢ ሽፋን ያለውን አገልግሎት ሊሰጥ ካልቻለ Amerigroup DC ከመረብ ውጪ ከሆነ አቅራቢ ሽፋን ያላቸውን አገልግሎቶችን በበቂ እና በትክክለኛ ጊዜ ይሰጣል።

**ቀጠሮ ማስያዝ**

**የእርስዎPCP ጋር ቀጠሮ ማስያዝ**

- የተመዝጋቢID ካርድዎን እና እርሳስ እና ወረቀት አጠገብዎ ያድርጉ።
- የእርስዎPCP ቢሮ ጋር ይደውሉ። በተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎ ፊት ገጽ ላይ የእርስዎንPCP የስልክ ቁጥር ይፈልጉ። በተጨማሪም በእርስዎ የአቅራቢID ኦንላይን በ **myamerigroup.com/DC** ሊያገኙት ይችላሉ።
- ስልኩን ለሚያነሱት ግለሰብ እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ እንደሆኑ ይንገሯቸው። የእርስዎPCP ጋር ቀጠሮ መያዝ እንደፈለጉ ይንገሯቸው።

- ቀጠሮ መያዝ ለምን እንዳስፈለግዎት ለግለሰቡ ይንገሯቸው። ለምሳሌ፥
    a. ህመም እየተሰማዎ ነው።
    b. እራስዎን ጎድተዋል ወይም አደጋ አጋጥምዎታል
    c. ምርመራ ወይም የክትትል ምርመራ ያስፈልግዎታል

- የቀጠሮዎን ጊዜ እና ቀን ይጻፉት።

- በቀጠሮዎ ቀን በሰዓቱ ይገኙ እና የተመዝጋቢID ካርድዎን እና ፎቶግራፍ ያለው መታወቂያ ይያዙ።

- ቀጠሮ ለማስያዝ እርዳታ ካስፈለጎት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

**ቀጠሮ መቀየር ወይም መሰረዝ**

- በቀጠሮዎ መገኘት እና በሰዓቱ መምጣት በጣም አስፈላጊ ነው።
- ቀጠሮዎን መቀየር ወይም መሰረዝ ካለብዎ፣ እባክዎ ከቀጠሮዎ 24 ሰዓታት በፊት ወደ ሐኪምዎ ይደውሉ።
- ለአንዳንድ ቀጠሮዎች፣ ለመሰረዝ ከ 24 ሰዓታት የበለጠ ቀደም ብለው መደወል ሊኖርብዎ ይችላል።
- በቀጠሮዎ ላይ ካልተገኙ ወይም ከዘገዩ፣ ሐኪምዎ ታካሚያቸው እንደማይሆኑ ሊወስኑ ይችላሉ።

**የእርስዎ የPCP ወይም የPDP ቢሮ ዝግ በሚሆንበት ጊዜ ህክምና ማግኘት**

ቢሮው ዝግ በሚሆንበት ጊዜ የእርስዎንPCP ወይምPDP ማናገር ካስፈለግዎ፣ የእርስዎPCP ወይምPDP ቢሮ ጋር ይደውሉ እና ስልኩን የሚያነሱት ግለሰብ ጋር መልእክትዎን እና ስልክ ቁጥርዎን ያስቀምጡ። በተቻለ ፍጥነት አንድ ሰው ይደውልልዎታል። ወደ911 ይደውሉ ወይም የድንገተኛ ሕክምና ክፍል ይሂዱ፣ ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠመዎት። እንዲሁም፣ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ የስልክ መስመር (24-hour Nurse Help Line) ላይ በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል?**

በደወሉ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ የሐኪምዎ ቢሮ ለእርስዎ ቀጠሮ ይሰጥዎታል። በእነዚህ ጊዜያት ቀጠሮ ማግኘት ካልቻሉ እባክዎ ወደ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ። ከታች ያለው ሰንጠረዥ ቀጠሮ ለማግኘት ምን ያክል ጊዜ እንደሚፈጅ ያሳያል።

| የጉብኝት ዓይነት | የእርስዎ ሁኔታ | ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? |
|---|---|---|
| **አስቸኳይ ጉብኝት** | ተጎድተዋል ወይም ታመዋል እና እንዳይብስብዎ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ሕክምና ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አሁኑኑ ሐኪም ማየት አያስፈልግዎትም። አንዳንድ ምሳሌዎች አነስተኛ ቃጠሎዎች፣ የራስ ምታት፣ የጉሮሮ ህመም፣ ወይም የጡንቻ መሸማቀቅ/መወጠር ናቸው። | በ 24 ሰዓታት ውስጥ |
| **መደበኛ ጉብኝት** | አነስተኛ ህመም ወይም ጉዳት አለብዎ ወይም መደበኛ ምርመራ ያስፈልግዎታል፣ ነገር ግን አስቸኳይ ቀጠሮ አያስፈልግዎትም። | በ 30 ቀናት ውስጥ |
| **የክትትል ጉብኝት** | ከህክምናው በኋላ ዶክተርዎን ማየት ያስፈልግዎታል። በደንብ እየተሻሎት መሆኑን ብቻ ማረጋገጥ አለብት። | ከ 1-2 ሳምንታት ውስጥ፣ እንደ ሕክምናው ዓይነት |
| **የአዋቂ የደህንነት ምርመራ ጉብኝት** | • አዲስ ሐኪም ጋር የመጀመሪያ ቀጠሮዎን እየያዙ ነው<br>• መደበኛ የአዋቂ ምርመራዎ ደርሷል<br>• የፕሮስቴት ምርመራ፣ የፔልቪክ ምርመራ፣ የPAP ስሚር፣ ወይም የጡት ምርመራዎ ደርሷል | በ 30 ቀናት ውስጥ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ከዚያ በፊት |

| የጉብኝት ዓይነት | የእርስዎ ሁኔታ | ሐኪምዎን ለማየት ምን ያክል ጊዜ ይፈጃል? |
|---|---|---|
| ስፔሺያሊስቶች ጋር አስቸኳይ ያልሆኑ ቀጠሮዎች (በሪፈራል) | የእርስዎPCP አስቸኳይ ላልሆነ ሁኔታዎ ስፔሺያሊስት እንዲያዩ ሪፈር አድርጎዎታል። | በ 30 ቀናት ውስጥ |

<u>የድጋፍ አገልግሎቶች</u>

**የትራንስፖርት አገልግሎቶች**

ድንገተኛ ላልሆኑ ሁኔታዎች ወደ ሐኪም ቀጠሮ እና ወደ መድሃኒት ቤት ለመሄድ የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል።

- Medical Transportation Management (MTM) ጋር በ888-828-1081 ይደውሉ እና ስንት ሰዓት ላይ እና የትኛው ቀን ላይ እንዲያደርስዎ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው።
- ትራንስፖርት ለማግኘት ከቀጠሮዎ ቢያንስ ከሁለት የሥራ ቀን በፊት (ቅዳሜን እና እሁድን አይጨምርም) መደወል አለብዎ። ወደEPSDT ጉብኝቶች እና አስቸኳይ ለሆኑ ጉብኝቶች ትራንስፖርት የሚያስፈልግዎ ከሆነ፣ ትራንስፖርት ለመጠየቅ ከቀጠሮው ቀን በፊት መደወል ይችላሉ።
- የትራንስፖርቱ ዓይነቶች Uber፣ Lyft፣ ባሶች፣ ሜትሮ፣ ለታክሲ የሚከፍሉት ደረሰኞች፣ የዊልቼይር ቫኖች፣ እና አምቡላንሶች ናቸው። የሚያገኙት የትራንስፖርት ዓይነት የሚወሰነው በሚያስፈልግዎ የሕክምና ዓይነት ነው።
- ለMTM የተመዝጋቢID ካርድዎን፣ የስልክ ቁጥርዎን፣ እና የሚነሱበትን ቦታ አድራሻ ይስጧቸው። በተጨማሪ፣ የሚሄዱበትን የሕክምና/የጥርስ ሕክምና ተቋም ወይም የሐኪም ቢሮ ስም፣ አድራሻ፣ እና ስልክ ቁጥር ይንገሯቸው።

Amerigroup DC በAmerigroup DC ላልተሸፈኑ ነገር ግን በDHCF ወይም በሌላ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች ለተሸፈኑ የሐኪም ቀጠሮዎች የደርሶ መልስ ትራንስፖርት ይሰጣል። በተጨማሪ Amerigroup DC ለአብዛኛዎቹ ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች ወደ/ከ ትራንስፖርት ያቀርባል።

**የአስተርጓሚ እና የትርጉም አገልግሎቶች/አገልግሎቶች መስማት እና ማየት ለተሳናቸው**

**የአስተርጓሚ አገልግሎቶች**
Amerigroup DC በሆስፒታሉ ውስጥ ጨምሮ የቃል የትርጉም አገልግሎቶችን በነጻ ይሰጣል።

እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ ለአስተርጓሚ አገልግሎቶች። የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ ከሐኪም ቀጠሮዎ በፊት ያግኙን።

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት በስልክ ነው። የሐኪም ቀጠሮዎ ላይ አስተርጓሚ ከእርስዎ ጋር እንዲገኙ ካስፈለጎት፣ በ 3-5 ቀናት ውስጥ ወይም በ 48 ሰዓታት ውስጥ ለኛ ማሳወቅ አለብዎ። በአካል ፊት ለፊት የትርጉም አገልግሎትን የሚያስፈልግ ልዩ ሁኔታ ካለ፣ ተመዝጋቢዎቹ ወይም አቅራቢዎቹ ከAmerigroup DC የቅድሚያ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው። ተመዝጋቢዎች ወይም አቅራቢዎች የፈቃድ ጥያቄን ከቀጠሮ ቀን በፊት ለማስገባት የኛን የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ቡድንን ማነጋገር ይችላሉ።

**የትርጉም አገልግሎቶች**
ከAmerigroup DC መረጃ ካገኙ እና ወደ ሌላ ቋንቋ እንዲተረጎምልዎ ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**መስማት እና ማየት ለተሳናቸው ተጨማሪ የድጋፍ አገልግሎቶች**
የመስማት ችግር ካለብዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር TTY 711። የማየት ችግር ካለብዎት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)። መረጃን በኦዲዮ ቴፕ፣ በብሬል ወይም በትልቅ እትመት ልንሰጥዎት እንችላለን።

## <u>የስፔሺያሊቲ ህክምና እና ሪፈራል</u>

### የስፔሺያሊቲ ሕክምና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል

የእርስዎ ዋና የእንክብካቤ አቅራቢ (PCP) አብዛኛውን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን ሊያሟላ ይችላል፣ ነገር ግን ከሌላ የአቅራቢዎች አይነት እንክብካቤ ሊፈልጉ ይችላሉ። እኛ ለህክምና አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች እንክብካቤዎችን ከሚሰጡ ከተለያዩ አይነት አገልግሎት ሰጪዎች አገልግሎት እንሰጣለን። እነዚህ አቅራቢዎች በልዩ የሕክምና መስክ ልዩ ስልጠና ስለወሰዱ ስፔሻሊስቶች ተብለው ይጠራሉ።

የስፔሻሊስቶች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፥

- አለርጂስትስ (የአለርጂ እና የአስም ሐኪሞች)
- ዴርማቶሎጂስት (የቆዳ ሐኪሞች)
- ካርዲዮሎጂስት (የልብ ሐኪሞች)
- ኢንዶክሪኖሎጂስት (የስኳር በሽታ እና የታይሮይድ ሐኪሞች)
- ፖዲያትሪስቶች (የእግር ሐኪሞች)
- ኦንኮሎጂስት (የካንሰር ሐኪሞች)
- ኦብስቴትሪክስ/ጋይናኮሎጂ (የጽንስና የማህፀን ሕክምና) (OB/Gyn)

ስፔሺያሊስት ማየት ከፈለጉ፣ ነገር ግን Amerigroup DC ለጉብኝቱ ክፍያ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ያለ ሌላ ሐኪም ጋር ቀጠሮ በማስያዝ ሁለተኛ አስተያየት ያግኙ
- በውሳኔያችን ላይ ይግባኝ ያቅርቡ (ገጽ 31 ይመልከቱ በይግባኝ ላይ)
- ፍትሃዊ ችሎት ይጠይቁ (ገጽ 30 ይመልከቱ ስለ ፍትሃዊ ችሎቶች)

### የራስ-የሪፈራል አገልግሎቶች
የተወሰኑ አገልግሎቶችን ያለቅድመ ፈቃድ ከእርስዎPCP ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ የራስ የሪፈራል አገልግሎቶች ተብለው ይጠራሉ እና ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

**ለሚከተሉት ሪፈራል አያስፈልግዎትም፥**
- የእርስዎንPCP ለማየት
- ድንገተኛ ጉዳይ ሲያጋጥምዎ ሕክምና ለማግኘት
- ለመደበኛ ወይም የመከላከል አገልግሎቶች በመረብዎ ውስጥ ያሉ የእርስዎ የአዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም (OB/GYN) አገልግሎቶች ለማግኘት (ለሴቶች ብቻ)
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች (STIs) አገልግሎቶች ለማግኘት
- ክትባቶች (መርፌዎች) ለማግኘት
- በመረብ ውስጥ የሚገኝ የዓይን ሕክምና አቅራቢ ጋር ለመሄድ

**የባህሪ ጤና (የአእምሮ ጤና ወይም የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መታወክ አገልግሎቶች)**
የባህሪ ጤና አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት የእርስዎንPCP ማየት **አያስፈልግዎትም**። ነገር ግን፣ በእኛ አውታረ መረብ ውስጥ ካለ ሰው የእርስዎን እንክብካቤ ማግኘት ያስፈልግዎታል። አሁን እንክብካቤ እያገኙ ከሆነ፣ አቅራቢዎን **Amerigroup DC**ን እንደሚወስዱ ይጠይቁ።

ከመጀመሪያው ጉብኝትዎ በፊት፥
1. የቀድሞ ዶክተርዎ መዝገቦችዎን ወደ አዲሱ አገልግሎት ሰጪዎ እንዲልክ **ይጠይቁት**። ይህ ምንም አያስከፍልዎትም። አገልግሎት ሰጪዎ ስለ ፍላጎቶችዎ እንዲያውቅ ይረዳሉ።
2. ከአዲሱ አገልግሎት አቅራቢዎ ጋር ቀጠሮ ለመያዝ ሲደውሉ **የAmerigroup DC ካርድዎን ያዘጋጁ**።
3. **የAmerigroup DC** ተመዝጋቢ መሆንዎን ይናገሩ እና የእርስዎን **Medicaid ID ቁጥር** ይስጡ።
4. የቀጠሮዎን ቀን እና ሰዓት **ይፃፉ**። አዲስ ታካሚ ከሆኑ፣ አቅራቢው ቶሎ እንዲመጡ ሊጠይቅዎት ይችላል። እዚያ እንድገኙ የጠየቁዎትን ጊዜ ይጻፉ።
5. አገልግሎት ሰጪዎን ለመጠየቅ የሚፈልጓቸውን ጥያቄዎች **ዝርዝር ያዘጋጁ**። ያጋጠሙዎትን ማንኛውም ችግሮች ይዘርዝሩ።

**በቀጠሮው ቀን፥**
1. አገልግሎት ሰጪዎ **እንዴት እንደሚረዳዎት** እንዲያውቅ ሁሉንም መድሃኒቶችዎን እና የጥያቄዎችን ዝርዝር ከእርስዎ ጋር **ይዘው ይሂዱ**።
2. ለጉብኝትዎ **በሰዓት ይገኙ**። ቀጠሮዎን ማክበር ካልቻሉ፣ እባክዎ አዲስ ጊዜ ለማግኘት ለአገልግሎት ሰጪዎ ይደውሉ።
3. **የAmerigroup DC መታወቂያ ካርድዎን** ከእርስዎ ጋር **ይዘው ይሂዱ**። አገልግሎት አቅራቢዎ ቅጂ ሊያደርግ ይችላል።

በመደወል የባህሪ ጤና እና/ወይም የቁስ አጠቃቀም መታወክ እርዳታ ወዲያውኑ ማግኘት ይችላሉ**800-600-4441 (TTY 711)፥** ለእርስዎ/ልጅዎ ምርጡን አቅራቢ እንዲያገኙ እንረዳዎታለን። 24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት መደወል ይችላሉ።

**9-1-1** ላይ መደወል አለብዎት፣ እርስዎ/ልጅዎ ለሕይወት አስጊ የሆነ የባህሪ ጤና ድንገተኛ ሁኔታ እያጋጠማችሁ ከሆነ። እንዲሁም ወደ ቀውስ ማእከል ወይም በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የድንገተኛ ክፍል መሄድ ይችላሉ። እርዳታ ለማግኘት ድንገተኛ ሁኔታ መጠበቅ አያስፈልግዎትም።

ወደ **9-8-8** መደወል ይችላሉ። **የ988** ራስ ማጥፋት እና ቀውስ የህይወት-መስመር ራስን የማጥፋት ወይም ከባህሪ ጤና ጋር በተዛመደ ጭንቀት ውስጥ ላሉ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም ስጋቶች ላሉባቸው ሰዎች የ 24/7 ሚስጥራዊ ድጋፍ ይሰጣል።
- የሞባይል ቀውስ አገልግሎቶች (ልጆች/ወጣቶች) CHAMPS በ202-481-1440 - በሳምንቱ ውስጥ የባህሪ ወይም የአዕምሮ ጤና ችግር ለሚገጥማቸው ልጆች፣ በቤት፣ በትምህርት ቤት ወይም በማህበረሰብ ውስጥ የሞባይል በቦታው ላይ የድንገተኛ እርዳታ ይሰጣል። አገልግሎቶቹ ከ 6-21 አመት ለሆኑ ህጻናት እና ወጣቶች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ቅዳሜና እሁድ፣ እባክዎ ለማህበረሰብ ምላሽ ቡድን ይደውሉ።
- የቅድመ ልጅነት የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች (Healthy Futures) በ202-698-1871 - ዕድሜያቸው እስከ 5 ዓመት ለሆኑ ህጻናት የችግር ጣልቃገብነት እና የድጋፍ ማእከል ሰራተኞች በግለሰብ የልጆች ባህሪ እና የክፍል አስተዳደር ላይ ያቀርባል።

ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆነ፣ **ለAmerigroup DC የአስተርጓሚ አገልግሎት የስልክ መስመር** መደወል ይችላሉ።
መስማት የተሳነዎት ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት፣ እባክዎ ወደ **TTY 711** ይደውሉ።

**የአልኮል መጠጥ ወይም ሌሎች የአደንዛዥ እጽ ችግር አገልግሎቶች**

የአልኮል መጠጥ ወይም ሌላ የአደንዛዥ እጽ ችግሮች ለጤናዎ አደገኛ ነው እና አቅራቢያዎ ላሉ ሰዎች ጤናም አደገኛ ሊሆን ይችላል። ለእነዚህ ችግሮች እርዳታ ካስፈለጎት ወደ ሐኪም መሄድ አስፈላጊ ነው። Amerigroup DC የዲቶክስፊኬሽን (የጸረ መርዛማነት) አገልግሎቶችን በማመቻቸት ይረዳዎታል እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያግዝዎ የእንክባካቤ ቅንጅትን ያቀርብልዎታል። አገልግሎቶችን ለማግኘት እና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚረዱ የእንክብካቤ ማስተባበርን ለማቅረብ። ለእነዚህ ችግሮች አገልግሎቶችን ለማግኘት፣ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፥

- የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ**800-600-4441** 24 ሰዓታት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት ይደውሉ።
- የግምገማ እና ሪፈራል ማእከል (Assessment and Referral Center, ARC) በቀጥታ ወይም 75 Florida Ave. NE, Washington, DC 20002 በመጎብኘት ያግኙ። የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም መታወክ ህክምና ለሚፈልጉ ግለሰቦች የተመሳሳይ ቀን ግምገማ እና ሪፈራል ያቀርባል፣ ይህም መመረዝን መቆጣጠር፣ በመድሃኒት የታገዘ ህክምና እና የግለሰብ እና የቡድን ምክርን ይጨምራል።
- የDC ማረጋጊያ ማዕከል (DC Stabilization Center) - 35 K St. NE, Washington, DC 202-839-3500 - በአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም ቀውስ ውስጥ ላሉ ሰዎች የሚፈልጉትን እርዳታ ለማግኘት ደህንነቱ የተጠበቀ ቦታ ይሰጣል፣ እና የተፈቀደላቸው መድኃኒቶችን በቦታው ይሰጣል፣ ማማከር እና ሪፈራል እና የረጅም ጊዜ የሕክምና አማራጮችን ይሰጣል። 24 ሰዓት በቀን፣ 7 ቀናት በሳምንት ክፍት ነው።

ሁሉም የባህሪይ ጤና፣ የአልኮል መጠጥ፣ እና የአደንዛዥ እጽ ሱስ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

<u>የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች</u>

የወሊድ መቆጣጠሪያ ወይም ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ሁሉም የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሚስጥራዊ ናቸው።

የወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ እቅድ አገልግሎቶችን በAmerigroup DC አቅራቢ መረብ ውስጥ ከሚገኝ ሐኪም ማግኘት ይችላሉ። እነዚህን አገልግሎቶች ለማግኘት ሪፈራል አያስፈልግዎትም። ከእርስዎPCP ውጪ ሌላ የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሐኪም ከመረጡ፣ ለእርስዎPCP ይንገሯቸው። የእርስዎPCP ለእርስዎ የተሻለ እንክብካቤ እንዲሰጡ ያግዛቸዋል። ከእርስዎPCP ጋር ይነጋገሩ ወይም ወደ Amerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ፣ ለወሊድ መቆጣጠሪያ እና ሌሎች የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ።

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፥**

- የእርግዝና ምርመራ
- የወሊድ ምርመራ እና ሕክምና*
- ለሴቶች እና ለጥንዶቹ የምክር አገልግሎት
- መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ
- የምክር አገልግሎት እና ክትባቶች
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ
- በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ሕክምና
- የማምከን ሕክምና (21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን ያስፈልጋል እና ከሕክምናው 30 ቀናት በፊት ቅጹን መፈረም ይጠይቃል)
- የHIV/AIDS ምርመራ እና የምክር አገልግሎት
- **DC Healthcare Alliance ለተመዝጋቢዎች የመካንነት ምርመራ እና ሕክምናን ይሸፍናል።*

**የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች የሚከተሉትን አያካትቱም፥**

- መደበኛ የመሃንነት ምርመራዎች ወይም ሕክምናዎች
- ለማምከን ማህጸንን ማውጣት
- በፈቃደኝነት የተከናወነ መሃንነትን ለመለወጥ
- HIV/AIDS
- ጽንስ ማስወረድ

**HIV/AIDS ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት፣ እና ሕክምና**

HIV/AIDS ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎቶች ሲኖሮት
- ከራስዎPCP
- ከHIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ማዕከል

የHIV ምርመራ እና የምክር አገልግሎት የት ማግኘት እንደሚችሉ መረጃ ለማግኘት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)። የHIV ሕክምና ካስፈለገዎት፣ የእርስዎPCP ሕክምና እንዲያገኙ ያግዝዎታል። ወይም ለ800-600-4441 (TTY 711) መደወል ይችላሉ። በተጨማሪ ሐኪምዎ ለHIV/AIDS ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳሎት ካመኑ የቅድመ መጋለጥ ፕሮፊላክሲስ (PrEP) ማግኘት ይችላሉ።

**<u>የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች እና በሐኪም የሚታዘዙ መድሃኒቶች</u>**

መድሃኒት ቤቶች (ፋርማሲዎች) መድሃኒትዎን የሚያገኙበት ቦታ ነው። ሐኪምዎ የመድሃኒት ማዘዣ ከሰጠዎት፣ በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ወዳለ መድሃኒት ቤት መሄድ አለብዎት።

በእርስዎAmerigroup District of Columbia የአቅራቢ ማውጫ ውስጥ ካለው በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም የመድሃኒት ቤቶች ዝርዝር ወይም ኦንላይን በ **<u>myamerigroup.com/dc/care/find-a-doctor.html</u>** ማግኘት ይችላሉ።

ከከተማ ውጪ ከሆኑ፣ ድንገተኛ ሕክምና፣ ወይም አስቸኳይ ሕክምና ካስፈለገዎት፥

- እየተጓዙ ከሆነ እና መድሃኒትዎን አስቀድመው መሙላት ከፈለጉ፣ የእረፍት ጊዜ አቅርቦት ለመጠየቅ የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች ጋር በ833-214-3604 (TTY 771) ይደውሉ።
- ለድንገተኛ አገልግሎት፣ በአቅራቢያዎ ወደሚገኝ የሆስፒታል ድንገተኛ ክፍል ይሂዱ ወይም ወደ911 ይደውሉ።
- ለአስቸኳይ ሕክምና፥
  - የእርስዎPCP ጋር ይደውሉ። የእርስዎ የPCP ቢሮ ዝግ ከሆነ፣ ሊገኙ የሚችሉበትን የስልክ ቁጥር ይተዉ። የእርስዎPCP ወይም ተተኪው ባለሞያ መልሰው ይደውልልዎታል።
  - የእርስዎንPCP ምክር ያክብሩ። ሕክምናውን በምን ያህል ፍጥነት ማግኘት እንዳለብዎት እና ሕክምናውን የት እንደሚያገኙ ሊነገርዎት ይችላል።
  - እርዳታ ከፈለጉ የ 24-ሰዓት የነርስ የእርዳታ መስመር (24-hour Nurse Help Line) ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**የሐኪም ማዘዣዎን ለማስሞላት፥**

- የAmerigroup DC መረብ አካል የሆነ እና ለሥራዎ ወይም ለቤትዎ ቅርብ የሆነ መድሃኒት ቤት ይምረጡ።
- የሐኪም ማዘዣ ካሎት፣ ወደ መድሃኒት ቤቱ ይሂዱ እና ለፋርማሲስቱ የሐኪም ማዘዣዎን እና የእርስዎን የAmerigroup DC የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድ ይስጧቸው።
- እርዳታ ካስፈለገዎት፣ እባክዎ ወደ የመድሃኒት ቤት የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ833-214-3604 (TTY 711) ይደውሉ።

**ማስታወስ የሚያስፈልጉ ነገሮች፥**

- ለመድሃኒቶችዎ እንዲከፍሉ መጠየቅ የለብዎትም። መድሃኒት ቤቱ ወይም የመድሃኒት መደብሩ እንዲከፍሉ ከጠየቅዎ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ ሐኪምዎ ለመድሃኒት ከAmerigroup DC የቀደመ ፈቃድ (PA) ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ሐኪምዎ የቀደመ ፈቃዱን (PA) ለማግኘት በሚጠባበቁበት ጊዜ፣ እርስዎ መድሃኒቱን የማግኘት መብት አሎት፥
    - እስከ 72 ሰዓታት ወይም
    - ወይም የመድሃኒቱን አንድ የተሟላ ዙር፣ በቀን ከአንድ ጊዜ ያነሰ የሚወስዱት ከሆነ

**መድሃኒትዎን ካልተቀበሉ፥**

- ዛሬ መድሀኒትዎን እንዳያገኙ የሚከለክልዎ ጉዳይ መፍትሄ እስኪያገኝ ድረስ ለሶስት ቀናት የሚቆይ የመድሃኒት አቅርቦትን ከፋርማሲስትዎ መጠየቅ ይችላሉ።
- በሐኪም የታዘዙትን መድሃኒቶች እና ምክንያቱን መቀበል ካልቻሉ ፋርማሲዎ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይሰጣል።
- አስተዳደራዊ ፍትሃዊ ችሎት ከመጠየቅዎ በፊት የሚተዳደረው የእንክብካቤ እቅድዎ የሚያቀርባቸውን ሁሉንም የውድቅ ማድረጊያ ሂደቶች ማጠናቀቅ አለብዎት።
- የመድሃኒት ጥያቄዎ አግባብ ባልሆነ መንገድ ውድቅ የተደረገ ወይም የተቀነሰ ከመሰለዎት የአስተዳደር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። ፍትሃዊ ችሎት ለመጠየቅ፥
    - ለDHCF እንባ ጠባቂ በ202-724-7491 ይደውሉ ወይም ወደ healthcareombudsman@dc.gov ኢሜይል ይላኩ
    - ወደ አስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ ይደውሉ በ202-442-9094
    - ወይም 441 4th Street, NW, Suite 450 North, Washington, DC 20001 ይጎብኙ

**በሽታ መቆጣጠር**

እርስዎ ከባድ በሽታ ካለብዎ ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጎት፣ የኛ የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም ውስጥ ልናስገባዎ እንችላለን። ይህ ማለት የበሽታ ተቆጣጣሪ ይኖርዎታል ማለት ነው። የበሽታ ተቆጣጣሪ የሚሰራው ለAmerigroup DC ነው እና በሽታዎን ለመቆጣጠር እና ጤናማ ለመሆን የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶች እና መረጃ እንዲያገኙ ያግዝዎታል።

**የህክምና ቅንጅት እና የጉዳይ ፍሰት ፕሮግራሞች**

እርስዎ ከባድ በሽታ ካለባችሁ ወይም ለስኳር በሽታ፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ የአእምሮ ጤና፣ ወይም አስም ለመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና ካስፈለጎት፥ Amerigroup DC የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችዎን የሚያግዙ ልዩ አገልግሎቶችን እና ፕሮግራሞችን ሊያቀርብልዎ ይችል ይሆናል። እርስዎ በሽታችዎን ለመቆጣጠር እና ጤናዎን ለማሻሻል የሚያስፈልግዎትን አገልግሎቶች እና መረጃ እንዲያገኙ ለማስቻል የጤና ሕክምና አስተዳዳሪ ይኖርዎታል።

የAmerigroup DC የሕክምና አስተዳዳሪ ለእርስዎ እና ለልጅዎ በሚከተሉት ላይ ያግዝዎታል፥

- የእርስዎን የተሸፈኑ አገልግሎቶች ማግኘት እና መረዳት፤
- የሕክምና ቀጠሮዎች እና ምርመራዎችን ማዘጋጀት፤
- ትራንስፖርት ማዘጋጀት፤
- ትክክለኛውን አገልግሎት ማግኘትዎን ለማረጋገጥ የተለያዩ ዘዴዎችን መፈለግ፤
- ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶችን ለመርዳት ግብዓቶችን መፈለግ እና ተንከባካቢዎችዎ የዕለት ተዕለት ጭንቀቶችን እንዲቋቋሙ መርዳት፤ እና
- የማህበረሰብ እና ማህበራዊ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት።

የእኛ ሰራተኞች ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎት ይችላሉ። እነሱ በተጨማሪ በአሁን ወቅት ለየትኞቹ ፕሮግራሞች እርስዎ እንደተመዘገቡ ሊያሳውቅዎ ይችላሉ። በተጨማሪም ሪፈራል ወይም ከአንድ ፕሮግራም ለመውጣት መጠየቅ ይችላሉ። ለበለጠ መረጃ፣ Amerigroup DC የህክምና አስተዳደር ፕሮግራምን በ833-346-1663 ያነጋግሩ።

## <u>አዋቂ ሰዎችን ከመታመም የሚከላከሉ አገልግሎቶች</u>

Amerigroup DC ጤናዎን እንዲጠብቁ ይፈልጋል። እኛ በተጨማሪ የኛ የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች ጋር እንዲመዘገቡ እንፈልጋለን። የጤና እና የደህንነት አገልግሎቶች የማጣሪያ ምርመራዎችን፣ የምክር አገልግሎት እና ክትባቶችን ያካትታሉ።

### የክትትል ምርመራዎች ምክረሀሳቦች (“ማጣሪያዎች”)

እባክዎ ቀጠሮ ይያዙ እና ለክትትል ምርመራ በየአመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ የእርስዎPCP ጋ ይሂዱ። በክትትል ምርመራዎ ወቅት ከእርስዎPCP ጋር ሊያወሯቸው ስለሚችሉ ነገሮች በ “የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች” ክፍል ላይ “የአዋቂ የደህንነት አገልግሎቶች” ዝርዝርን ይመልከቱ።

### የመከላከል የምክር አገልግሎት

የመከላከል የምክር አገልግሎት ለእርስዎ የሚቀርበው እርስዎ ጤናማ ሆነው እንዲቆዩ ለማስቻል ነው። በሚከተሉት ነገሮች ላይ የመከላከል የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፥

- ምግብ እና የአካል እንቅስቃሴ
- የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ መጠቀም
- ሲጋራ ማጨስ ማቆም
- የHIV/AIDS መከላከል
- የእርግዝና መከላከያ ሕክምና

### የአዋቂ ክትባቶች

አዋቂ ከሆኑ የተወሰነ ክትባቶች (መርፌዎች) ሊያስፈልግዎ ይችላል። የትኞቹ እንደሚያስፈልግዎ ለማወቅ እባክዎ የእርስዎ PCP ጋር ያውሩ።

## <u>እርግዝና - ልጅ መውለድ</u>

እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ የአዋላጅ ሐኪምዎ/የማህጸን ሐኪምዎ ጋር ወዲያውኑ መሄድ አስፈላጊ ነው። ይህን ቀጠሮ ከመያዝዎ በፊት የእርስዎን PCP ማየት አያስፈልግዎትም።

### እርጉዝ ከሆኑ፣ እባክዎ ይደውሉ፥

- የኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) በ202-727-5355 እርግዝናዎን ሪፖርት ለማድረግ
- የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711)
- የእርስዎPCP

እርጉዝ ከሆኑ ሊመረመሯቸው የሚገቡ የተወሰኑ ነገሮች አሉ። ይህ ጤናማ እርግዝና፣ ወሊድ፣ እና ህጻን እንዲኖርዎ ለማረጋገጥ ያግዛሉ። ይህ ቅድመ ወሊድ ሕክምና ተብሎ ይታወቃል። ህጻን ልጅዎ ከመወለዱ በፊት የቅድመ ወሊድ ሕክምና ያገኛሉ።

**ያስታውሱ፣ እርስዎ እርጉዝ ከሆኑ ወይም እርጉዝ ሊሆኑ እንደሚችሉ ካሰቡ፣ የአልኮል መጠጥ አይጠጡ፣ አደንዛዥ እጽ አይጠቀሙ፣ ወይም አያጭሱ።**

**የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ ሕክምና**

**ለነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች ልዩ እንክብካቤ**
Taking Care of Baby and Me® ለሁሉም ነፍሰ ጡር ተመዝጋቢዎች የAmerigroup DC ፕሮግራም ነው። ነፍሰ ጡር በሚሆኑበት ጊዜ የእርስዎን ዋና የእንክብካቤ አቅራቢዎን (PCP) ወይም የጽንስ እና የማህፀን ሐኪም (OB/GYN) ማየት በጣም አስፈላጊ ነው። አስቀድመው ልጅ የወለዱ ቢሆንም እንኳን የቅድመ ወሊድ እንክብካቤ ሁልጊዜ አስፈላጊ ነው። በፕሮግራማችን፣ ተመዝጋቢዎች የቅድመ ወሊድ እና የድህረ ወሊድ እንክብካቤ ለማግኘት መረጃ እና ሽልማቶችን ያገኛሉ።

በተጨማሪ የኛ ፕሮግራም የተወሳሰበ የሕክምና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸውን ነፍሰጡር ተመዝጋቢዎችንም ያግዛል። የነርስ የጉዳይ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉትን ለማቅረብ ከእነዚህ ተመዝጋቢዎች ጋር በቅርበት ይሰራሉ፦

- ትምህርት
- ስሜታዊ ድጋፍ
- የሐኪሞቻቸውን የእንክብካቤ እቅድ እንዲተገብሩ ማገዝ
- እንደ ማጓጓዣ፣ የሴቶች ጨቅላ ህጻናት እና ልጆች (WIC)፣ የቤት ውስጥ የጉብኝት ፕሮግራሞች፣ የጡት ማጥባት ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት የመሳሰሉ በማህበረሰብዎ ውስጥ ያሉ አገልግሎቶች እና ግብአቶች መረጃ

በተጨማሪ ነርሶች ከሐኪሞች ጋር ይሰራሉ እና ተመዝጋቢዎች ሊፈልጓቸው በሚችሉ ሌሎች አገልግሎቶች ላይ እገዛ ያደርጋሉ። ግቡ ለተመዝጋቢዎች የተሻለ ጤናን እና ጤናማ ሕፃናትን እንዲወለዱ ማድረግ ነው።

**ልጅዎን ከወለዱ በኋላ፣ ለተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) እናESA በ202-727-5355 ይደውሉ።**

## የእርስዎ የጤና ጥቅማጥቅሞች

**<u>በAmerigroup DC የሚሸፈኑ የጤና አገልግሎቶች</u>**

ከዚህ በታች ያለው ዝርዝር የሁሉንም የAmerigroup DC ተመዝጋቢዎች የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እና ጥቅማጥቅሞችን ያሳያል። ለአንዳንድ ጥቅማጥቅሞች፣ የተወሰነ የእድሜ ገደብ ላይ መሆን ወይም ለአገልግሎቱ ልዩ ፍላጎት ሊኖርዎ ይገባል። Amerigroup DC በመረብ ውስጥ ወዳለ አቅራቢ ወይም ሆስፒታል ከሄዱ፣ በዚህ ዝርዝር ውስጥ ላሉ ማንኛውም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ክፍያ አያስከፍልዎትም።

እርስዎ Amerigroup DC የተወሰነ የጤና እንክብካቤን የሚሸፍን መሆን አለመሆኑ ላይ ጥያቄ ካሎት፣ ወደ Amerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት |
| --- | --- |
| **የአዋቂ የደህንነት ምርመራ አገልግሎቶች** | • ክትባቶች<br>• በግብረስጋ ግንኙነት ለሚተላለፉ በሽታዎች መደበኛ የማጣሪያ ምርመራ<br>• የHIV/AIDS ማጣሪያ፣ ምርመራ፣ እና ምክር<br>• የጡት ካንሰር ምርመራ<br>• የማህጸን ካንሰር ምርመራ (ለሴቶች ብቻ)<br>• የኦስቲዮፖሮሲስ (አጥንት መሳሳት) ምርመራ (ለድህረ ማረጥ ለሴቶች)<br>• የHPV ምርመራ<br>• የፕሮስቴት ካንሰር ምርመራ (ለወንዶች ብቻ)<br>• የአብዶሚናል አኦርቲክ አኑሪዝም ምርመራ<br>• ከመጠን ያለፈ ውፍረት ምርመራ<br>• የስኳር በሽታ ምርመራ |

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት | |
|---|---|---|
| | • የከፍተኛ የደም ግፊት እና ኮሌስትሮል (የሊፒድ በሽታ) ምርመራ<br>• የድብርት ምርመራ<br>• የኮሎሬክታል ካንሰር ምርመራ (እድሜያቸው 50 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተመዝጋቢዎች)<br>• ሲጋራ የማጨስ የምክር አገልግሎት<br>• የምግብ እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የምክር አገልግሎት<br>• የአእምሮ ጤና የምክር አገልግሎት<br>• የአልኮል መጠጥ እና የአደንዛዥ እጽ ምርመራ | |
| **የባህሪ ጤና አገልግሎቶች** | • የምርመራ ግምገማ<br>• የቀውስ ሁኔታ አገልግሎቶች<br>• የምክር አገልግሎት<br>• ሳይኮቴራፒ<br>• የቴራፒ ቡድኖች<br>• Medical Transportation Management (MTM)<br>• የታካሚ መውጣት አስተዳደር/መርዝ ማውጣት<br>• የመኖሪያ ቤት ሕክምና | ሁሉም ተመዝጋቢዎች |
| **የጥርስ ሕክምና ጥቅማጥቅሞች** | ○ ጠቅላላ የጥርስ ሕክምና (መደበኛ እና የድንገተኛ ሁኔታ ህክምናን ጨምሮ) በየ 6 ወሩ የሚደረግ አጠቃላይ የጥርስ ምርመራን ጨምሮ የጥርስ እና የድድ እንክብካቤ እና ህክምና<br>○ ቀላል እና ውስብስብ የቀዶ ጥገና አገልግሎቶች እና መንቀል<br>○ ድንገተኛ የጥርስ ሕክምና<br>○ መሞላት<br>○ በየ 6 ወሩ ማጽዳት እና የፍሎራይድ ህክምናዎች<br>○ ለህክምና አስፈላጊ በሚሆንበት ከፊል ሰው ሰራሽ ጥርስ<br>○ ኤክስሬይ (በየ 3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ለ 1 ጊዜ የተሟሉ ተከታታይ)<br>○ ሰው ሰራሽ ጥርሶች (በየ5 ዓመቱ አንድ አዲስ ጥንድ) እና የሰው ሰራሽ ጥርስ ጥገና<br>○ የአፍ ውስጥ ቀዶ ጥገና<br>○ $1000 ገደብ በአንድ የካላንደር ዘመን ለሚሰጡ አገልግሎቶች | |
| **የዳይለሲስ (የኩላሊት እጥበት) አገልግሎቶች** | • በሳምንት እስከ 3 ጊዜያት ሕክምና (በቀን አንድ ጊዜ ብቻ) | |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME) እና አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS)** | • ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)<br>• አላቂ የሕክምና አቅርቦቶች (DMS) | |

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት |
|---|---|
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | • የእርግዝና ምርመራ፤ ለሴቷ የምክር አገልግሎት<br>• የወሊድ ምርመራ እና ሕክምና*<br>• መደበኛ እና ድንገተኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ<br>• በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ማምከን (ከቀዶ ጥገናው 30 ቀናት በፊት የተመዝጋቢው ፊርማ ያለው የጸደቀ የማምከን ቅጽ ያስፈልጋል)<br>• የማጣሪያ ምርመራ፣ የምክር አገልግሎት፣ እና ክትባቶች (ለሁማን ፓፒሎማ ቫይረስ- HPV ጨምሮ)<br>• በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ሁሉንም በሽታዎች ምርመራ እና የመከላከል ሕክምና<br>• ነርስ አዋላጅ ሐኪም እና የዳውላ አገልግሎቶች<br>• *DC Healthcare Alliance ለተመዝጋቢዎች የመካንነት ምርመራ እና ሕክምናን ይሸፍናል። |
| **የመስማት ጥቅማጥቅሞች** | • ከመስማት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ የመስሚያ መሳሪያዎች እና የመስሚያ መሳሪያ ባትሪዎች |
| **የቤት ውስጥ የጤና አገልግሎቶች** | • የቤት ውስጥ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፥<br>○ የነርሲንግ እና የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ እንክብካቤ<br>○ በቤት ጤና ኤጀንሲ የሚሰጥ የቤት ውስጥ የጤና እርዳታ አገልግሎቶች<br>○ የአካል ህክምና፣ኦኩፔሽናል ቴራፒ፣የንግግር ፓቶሎጂ እና የኦዲዮሎጂ አገልግሎቶች |
| **የሆስፒታል አገልግሎቶች** | • የተመላላሽ ታካሚ አገልግሎቶች (የመከላከል፣የመመርመሪያ፣ የሕክምና፣ የማገገሚያ ወይም የማስታገሻ አገልግሎቶች)<br>• የተኝቶ ታካሚ አገልግሎቶች (የሆስፒታል ቆይታ) |
| **ላቦራቶሪ እና የኤክስሬይ አገልግሎቶች** | • የላብራቶሪ ምርመራዎች እና ኤክስሬዮች |
| **የነርሲንግ ሆም እንክብካቤ** | • በነርሲንግ ሆም ውስጥ በሰለጠኑ ነርስ የሙሉ ጊዜ እንክብካቤ ለተከታታይ 30 ቀናት ድረስ ያክል |
| **የመድሃኒት ቤት አገልግሎቶች (የሃኪም ማዘዣ ያላቸው መድሃኒቶች)** | • በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች በAmerigroup DC የመድኃኒት ቀመር ውስጥ ተካትተዋል። የመድሃኒት ቅጹን በ **myamerigroup.com/DC** ወይም ለተመዝጋቢ አገልግሎቶች በመደወል ማግኘት ይችላሉ። |
| **የእግር በሽታ ሐኪም** | • ለእግር ችግሮች ልዩ ሕክምና<br>• በሕክምና አስፈላጊ ሲሆን መደበኛ የእግር ሕክምና |
| **ዋና የእንክብካቤ አገልግሎቶች** | • የመከላከል፣ ቀላል፣ እና ከባድ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በአጠቃላይ በእርስዎPCP የሚሰጥ |
| **የማገገሚያ አገልግሎቶች** | • ከባድ ጉዳት ወይም ሌሎች የሕክምና ክስተቶችን ተከትሎ አሰራርን ለማሻሻል ለመርዳት በሕክምና አስፈላጊ መሆኑን አስቀድሞ ፈቃድ የተሰጠ ሲሆን። ይህ የአካል፣ የንግግር፣ እና ኦኩፔሽናል ቴራፒን ያካትታል። |
| **የስፔሺያሊስት አገልግሎቶች** | • ልዩ ስልጠና በወሰዱ ሐኪሞች ወይም የላቀ ልምድ ባላቸው ነርሶች የሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች |

| ጥቅማጥቅም | እርስዎ የሚያገኙት |
|---|---|
| | • ሪፈራል አብዛኛውን ጊዜ ያስፈልጋል |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | • ወደ ሐኪም ቀጠሮዎች እና ከዚያ መልስ የትራንስፖርት አገልግሎት በDHCF የሚሸፈኑ አገልግሎቶችን ጨምሮ |

**ከፍያቸውን የማንሸፍነው አገልግሎቶች**

- ኮስሜቲክ የቀዶ ጥገና
- የሙከራ ወይም የምርመራ አገልግሎቶች፣ የቀዶ ጥገናዎች፣ ሕክምናዎች፣ እና መድሃኒቶች
- የክሊኒካል ሙከራ ፕሮቶኮል አካል የሆኑ አገልግሎቶች
- ጽንስ ማስወረድ፣ ወይም በፈቃደኝነት ጽንስን ማቋረጥ፣ በፌደራል ህጉ መሰረት የሚቻል አይደለም
- በሕክምና አስፈላጊ ያልሆኑ አገልግሎቶች
- ክፍት የልብ ቀዶ ጥገና
- የዓይን ሕክምና
- የሰውነት አካል ንቅለተከላ
- የተወሰኑ የምክር ወይም የሪፈራል አገልግሎቶች በሃይማኖታዊ ወይም የሞራል እምነቶች ምክንያት በAmerigroup DC ሽፋን ላይሰጣቸው ይችላል። ለበለጠ መረጃ፣ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶችን በ800-600-4441 ያነጋግሩ።

**የህክምና ሽግግር**

Amerigroup DC ለእርስዎ አዲስ ከሆነ፣ ለመጀመሪያ 90 ቀናት የተያዙትን የሐኪም ቀጠሮዎች እና የመድሃኒት ማዘዣዎችን እንዳሉ መቆየት ይችላሉ። አቅራቢዎ በአሁን ወቅት በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ካልሆኑ፣ በAmerigroup DC የአቅራቢ መረብ ውስጥ ያለ አዲስ አቅራቢ እንዲመርጡ ሊጠየቁ ይችላሉ። ሐኪምዎ የAmerigroup DC መረብን ከለቀቁ፣ ሌላ አቅራቢ ለመምረጥ ጊዜ እንዲኖርዎ በ 15 የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን። Amerigroup DC አቅራቢዎን ካቋረጠ፣ የሚያበቃበት ጊዜ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት በ 30 የካላንደር ቀናት ውስጥ እናሳውቅዎታለን።

**<u>ሌላ ጠቃሚ መረጃ</u>**

**ቦታ ከቀየርኩ ምን ማድረግ ይኖርብኛል**

- የመገኛ መረጃዎን በመስመር ላይ በ www.districtdirect.dc.gov ወቅታዊ ያድርጉ።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**ህጻን ልጅ ካለኝ ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**ህጻን ልጅ በማደጎ ከወሰድኩ ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።

**ከቤተሰቤ ውስጥ አንድ ሰው ቢሞት ምን ማድረግ አለብኝ**

- ለኢኮኖሚ ዋስትና አስተዳደር (ESA) የለውጥ ማዕከል በ202-727-5355 ይደውሉ።
- የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

**የእኔንMCP እንዴት መቀየር እንደምችል**

- የእርስዎንMCP በሚከተለው ሁኔታ መቀየር ይችላሉ፥
    - የመጀመሪያው የምዝገባ ቀንዎን ተከትሎ ባሉት 90 የካላንደር ቀናት ወይም ከዲስትሪክቱ የምዝገባ ማስታወቂያዎ ከደረሶት ከ 90 የካላንደር ቀናት በኋላ፣ ኋለኛው የሆነው የትኛውም።
    - በክፍት የምዝገባ ወቅት በዓመት አንድ ጊዜ።
    - ጊዜያዊ የብቃት ማጣት ክፍት የምዝገባ ወቅት እንዲያመልጥዎ ካደረገ።
    - ዲስትሪክቱMCP ላይ ቅጣት ከጣለ ወይም ምዝገባውን ካገደ።
        - ጥሩ ምክንያት/ሰበብ ካሎት በማንኛውም ጊዜ፣ ለምሳሌ፥ ከአገልግሎት መስጫ ክልል ከወጡ፤
        - Amerigroup DC በሞራል ወይም ሐይማኖታዊ ተቃውሞዎች ምክንያት፣ የሚያስፈልግዎትን አገልግሎት(ቶች) ካልሸፈነ፤
        - እርስዎ ተያያዥ አገልግሎቶችን በተመሳሳይ ጊዜ እንዲከናወን ከፈለጉ፣ እና ሁሉም ተያያዥ አገልግሎቶች ካልተገኙ፣ እና አቅራቢዎ አገልግሎቶቹን ለየብቻ ማግኘት አስጊ ነው ብለው ከወሰኑ
        - MCP የእርስዎን ዘር፣ ጾታ፣ ብሄር፣ ብሄራዊ ምንጭ፣ ሐይማኖት፣ የአካል ጉድለት፣ እርግዝና፣ እድሜ፣ የጄኔቲክ መረጃ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ጾታዊ መለያ፣ የግል አቀራረብ፣ የቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ የፖለቲካ ዝንባሌ፣ እና የገቢ ምንጭ ወይም የመኖሪያ አድራሻን መሠረት በማድረግ አድልዎ እንደፈጸሙብዎ ካመኑ፤ ወይም
        - ደካማ ጥራት ያለው ሕክምና ያገኙ ሆኖ ከተሰማዎት፣ ሽፋን ላላቸው አገልግሎቶች ተደራሽ አለመሆን፣ ወይም የእርስዎ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች ላይ ልምድ ያላቸው አቅራቢዎች ተደራሽ እንዳልሆኑ ከተሰማዎ።
- የD.C. ጤናማ ቤተሰቦች (D.C. Healthy Families) ከክፍት የምዝገባ ወቅት ሁለት ወራት በፊት ደብዳቤ ይልክልዎታል። ደብዳቤውMCPዎችን እንዴት መቀየር እንደሚችሉ ይነግርዎታል።
- የእርስዎንMCP ሲቀይሩ፣ የሚያስፈልግዎን እንክብካቤ ማግኘት እንዲቀጥሉ የእርስዎ የጤና እንክብካቤ መረጃዎ ወደ መረጡት አዲስMCP ይሸጋገራል።

**ከAmerigroup DC የጤና እንክብካቤ ማግኘት አይፈቀድልዎትም በሚከተሉት ሁኔታዎች፥**

- ለማንኛውም ሌላ የህክምና እርዳታ ፕሮግራም ወይም የጤና መድን ብቁ ከሆኑ።

.

**የD.C. መንግስት በሚከተሉት ምክንያቶች እርስዎን ከAmerigroup DC ሊያስወጣዎት ይችላል፥**

- የተመዝጋቢID ካርድዎን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ካደረጉ፤
- የጤና ሕክምና ማጭበርበር ከፈጸሙ፤ ወይም
- የተመዝጋቢ ግዴታዎችዎን ካላከበሩ።

**ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ሲደርስዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ**

ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ ለሆነ ሽፋን ላለው አገልግሎት የክፍያ መጠየቂያ ከደረሶት፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

**ሽፋን ለሌላቸው አገልግሎቶች መክፈል**

- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ማግኘት እንዳለብዎ ከወሰኑ እና ከAmerigroup DC የጽሁፍ ፈቃድ ከሌሎት፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ መክፈል ይኖርብዎታል።
- እኛ የማንከፍልበትን አገልግሎት ለማግኘት ከወሰኑ፣ ለአገልግሎቱ እራስዎ እንደሚከፍሉ መስማማትዎን የሚገልጽ መግለጫ መፈረም አለብዎ።
- አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ ***በፊት*** የተመዝጋቢ መታወቂያ ካርድዎን ማሳየት እና ለሐኪሞችዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን መንገር ሁሉጊዜ ያስታውሱ።

## የቀደመ መመሪያ

የቀደመ መመሪያ የሕክምና እንክብካቤዎን አስመልክቶ ስለእርስዎ በመሆን ምርጫዎችን የሚያደርግ ሰው እንዲመርጡ ያስችልዎታል። በተጨማሪ የቀደመ መመሪያ ፍላጎቶችዎን ለሌሎች ለመንገር በማያስችል ሁኔታ በጣም ቢታመሙ ምን ዓይነት የሜዲካል ሕክምና ማግኘት እንደሚፈልጉ ለመናገር ያስችልዎታል።

ስለ ቀደመ መመሪያዎ ከቤተሰብ፣ ከእርስዎPCP፣ ወይም እርስዎን ከሚያግዙ ሌሎች ሰዎች ጋር ማውራት ጠቃሚ ነው።

የቀደመ መመሪያ መሙላት እና መፈረም ከፈለጉ፣ በቀጣይ ቀጠሮዎ ላይ የእርስዎ PCP እንዲያግዝዎ ይጠይቋቸው፣ ወይም የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)፣ እና እነሱ እርስዎን ያግዛሉ።

## የሐኪም (ዶክተር) የጥቅማጥቅም እቅድ መግለጫ

እርስዎ Amerigroup DC ልዩ የፋይናንስ ትብብር ከAmerigroup DC ሐኪሞች ጋር ያላቸው መሆን ወይም አለመሆኑን የማወቅ መብት አለዎት።

እባክዎ ለዚህ መረጃ ወደ የAmerigroup DC የተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።

## ማጭበርበር ምንድን ነው?

ማጭበርበር ከባድ ጉዳይ ነው። ማጭበርበር ማለት የማይገባዎትን የተወሰነ ጥቅማጥቅምን ወይም ክፍያን ለማግኘት ሀሰተኛ መግለጫዎችን ወይም ፍሬ ነገሮችን መግለጽ ማለት ነው። የአቅራቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ፥ ላልተሰጡ አገልግሎቶች እና አቅርቦቶች የክፍያ ጥያቄ ማቅረብ። የተመዝጋቢዎች የማጭበርበር ምሳሌ ማለት የColumbia ዲስትሪክት ዙሪያ ውጪ እየኖሩ ኮሎምቢያ ውስጥ እንደሚኖሩ በሐሰት መግለጽ።

የማጭበርበር ድርጊትን ከጠረጠሩ፣ እባክዎ ለኛ ያሳውቁን። እራስዎን መግለጽ ወይም ስምዎን መስጠት አያስፈልግዎትም። ማጭበርበር ምን ምን እንደሚያካትት የበለጠ መረጃ ከፈለጉ፣ የAmerigroup DC ድረገጽን በ **myamerigroup.com/DC** ይጎብኙ። ማጭበርበርን ሪፖርት ለማድረግ፣ ይደውሉ ወደ Amerigroup DC የትግበራ የስልክ መስመር ጋር፣ **866-847-8247** ወይም የDC የጤና እንክብካቤ የፋይናንስ ማጭበርበር ዲፖርትመንት የስልክ መስመር ጋር በ**877-632-2873** ይደውሉ።

## ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች

Amerigroup DC እና የዲስትሪክቱ መንግስት ሁለቱም እርስዎ ስለሚያገኙት እንክብካቤ፣ ወይም Amerigroup DC ስለሚያቀርብልዎ አገልግሎቶች አቤቱታ የሚያቀርቡበት ዘዴ አላቸው። ቅሬታዎን ከዚህ በታች እንደተገለፀው ማቅረብ ይችላሉ።

### ቅሬታዎች

- እርስዎ ላይ በተፈጠረ አንድ ነገር ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። የሚከተሉት ቅሬታ ማቅረብ ሊያስፈልግዎ የሚችሉባቸው ምክንያቶችን ምሳሌ ያካትታሉ፥
  - በአክብሮት እንዳልተስተናገዱ ተሰምትዎታል
  - ባገኙት የጤና ሕክምና እንክብካቤ አልረኩም
  - ቀጠሮ ለማግኘት በጣም ረጅም ጊዜ ወስዷል
- ቅሬታ ለማቅረብ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 (TTY 711) መደወል አለብዎት።
- በተጨማሪ ሐኪምዎ ለእርስዎ ቅሬታ ሊያቀርብልዎት ይችላሉ።

ያልተደሰቱበት ነገር ከተፈጠረ በኋላ በማንኛውም ጊዜ ቅሬታ ማቅረብ ይችላሉ። Amerigroup DC አብዛኛውን ጊዜ በ 90 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል ነገር ግን ውሳኔ ለመስጠት ተጨማሪ ጊዜም ሊጠይቁ ይችላሉ (ነገር ግን በአጠቃላይ ከ104 የካላንደር ቀናት ሊበልጥ አይችልም)።

ቅሬታ በጽሁፍ Amerigroup DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ለ Centralized Appeals Processing | Amerigroup District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

**ይግባኞች**

- ጥቅማጥቅሞችዎ አለአግባብ እንደተከለከሉ፣ እንደተቀነሱ፣ እንደዘገዩ፣ ወይም እንደቆሙ ከተሰማዎ፣ Amerigroup DC ጋር ይግባኝ የማቅረብ መብት አሎት። ደውለው ይግባኝዎን በስልክ ካቀረቡ፣ Amerigroup DC ይግባኝዎን በደብዳቤ አጠቃለው ይጽፉታል እና ለእርስዎ ቅጂውን ይልካሉ። ደብዳቤውን በጥንቃቄ ማንበብዎን እና ለመዝገቦችዎ ማስቀመጥዎን እርግጠኛ ይሁኑ።
- ይግባኝዎ በደረሰ በ 30 የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎ ላይ በAmerigroup DC ውሳኔ ይሰጣል።
- Amerigroup DC መረጃ ለማግኘት ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለጋቸው እና ዲስትሪክቱ ይህ ለእርስዎ የሚጠቅም እንደሆነ ከወሰነ፣ ወይም እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ ተጨማሪ ጊዜ ከጠየቃችሁ፣ Amerigroup DC የውሳኔ ጊዜውን በ 14 የካላንደር ቀናት ሊጨምረው ይችላል። Amerigroup DC ስለ ማራዘሚያው የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጥዎ ይገባል።
- ፖስታው ላይ፣ ስለ ይግባኝዎ የAmerigroup DC የውሳኔ የጽሁፍ ማስታወቂያ ይደርስዎታል።
- Amerigroup DC በይግባኝዎ ላይ በሰጠው ውሳኔ ደስተኛ ካልሆኑ፣ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- Amerigroup DC ጋር ይግባኝ ለማቅረብ፣ ለተመዝጋቢ አገልግሎቶች በ800-600-4441 (TTY 711) ይደውሉ።
- ይግባኝን በጽሁፍ Amerigroup DC ጋር ለማቅረብ፣ በፖስታ ይላኩ ወደ Centralized Appeals Processing | Amerigroup District of Columbia, Inc. | P.O. Box 62429 | Virginia Beach, VA 23466-2429።

**ፍትሃዊ ችሎቶች**

እርስዎ Amerigroup DC ጋር ባቀረቡት ይግባኝ ውጤት ካልረኩ፣ የDC የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር "ፍትሃዊ ችሎት" መጠየቅ ይችላሉ።

የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄ ለማቅረብ፣ የዲስትሪክቱ መንግስት ጋር ይደውሉ ወይም ይጻፉ ወደ፥

District of Columbia Office of Administrative Hearings
Clerk of the Court
441 4th Street, NW
Room N450
Washington, DC 20001
የስልክ ቁጥር፥ 202-442-9094

**የመጨረሻ ቀናቶች፥**

- ጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያከተሰጠበት ቀን አንስቶ በ 60 የካላንደር ቀናት ውስጥ ይግባኝዎን ማቅረብ አለብዎ።
- የAmerigroup DC የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን ከ 120 የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- በፍትሃዊ ችሎትዎ ወይም ይግባኝዎ ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ማግኘት መቀጠል ከፈለጉ፣ ፍትሃዊ ችሎቱ ወይም የይግባኝ ችሎቱ ከሚከተለው ጊዜ በኋላ የሚከተሉትን እንዲያደርግልዎ መጠየቅ አለብዎት፥

- ○ በAmerigroup DC የጎጂ የጥቅማጥቅም ውሳኔ ማስታወቂያን በላከበት ፖስታ ላይ ካለው ቀን ወይም የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ካለው ቀን በ 10 የካላንደር ቀናት ወይም
- ○ የAmerigroup DC የታቀደው እርምጃ ተፈጻሚነቱ ከሚጀምርበት ቀን አንስቶ (ወይም፣ በሌላ አባባል፣ ጥቅማጥቅሙ የሚቆምበት ቀን)።

አቅራቢዎ እርስዎን በመወከል ይግባኝ ሊያቀርብልዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎት ሊጠይቅልዎ ይችላሉ።

**የተፋጠነ (ድንገተኛ) ቅሬታዎች እና የይግባኞች ሂደት**

ይግባኝዎ ድንገተኛ መሆኑ ከተወሰነ፣ Amerigroup DC በ 72 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥዎታል። አንድ ይግባኝ ድንገተኛ ነው ተብሎ የሚቆጠረው እርስዎ መደበኛውን የይግባኝ ሂደት የጊዜ ማዕቀፍ ቢጠብቁ ለእርስዎ ጎጂ ወይም የሚያሰቃይ ከሆነ ነው።

HIV/AIDS፣ የአእምሮ በሽታ፣ ወይም አፋጣኝ ትኩረት የሚፈልግ ሌላ ሁኔታ ባለባቸው ተመዝጋቢዎች የሚቀርቡ ሁሉም ይግባኞች ይግባኙ በቀረበ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ውሳኔ አግኝተው ለተመዝጋቢው ይገለጽላቸዋል።

**በቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ እና ፍትሃዊ ችሎቶች ሂደት ውስጥ እርስዎ ያሎት መብቶች**

- እርስዎ ፍትሃዊ ችሎት የማግኘት መብት አለዎት። እርስዎ Amerigroup DC ጋር አንድ ደረጃ ያለው የይግባኝ ሂደት ካቀረቡ በኋላ፣ ከአስተዳደር ችሎት ቢሮ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- የይግባኝ ውሳኔ ማስታወቂያውላይ ካለው ቀን አንስቶ ከ 120 የካላንደር ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ አለብዎት።
- Amerigroup DC ይግባኝዎን የሚመለከት ማስታወቂያ ካልሰጠዎት ወይም በጊዜ ማስታወቂያ ካልሰጠዎት፣ ከዚያ በኋላ የይግባኝ ሂደቱ የተሟላ እንደሆነ ይቆጠራል፣ እና መቀጠል እና ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ።
- ይግባኝዎ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ በሚታይበት ጊዜ የከለከልንዎትን ጥቅማጥቅም እያገኙ የመቆየት መብት አለዎት። በፍትሃዊ ችሎት ወቅት ጥቅማጥቅምዎን ይዞ ለመቆየት፣ በተወሰኑ ቀናት ውስጥ ፍትሃዊ ችሎቱን መጠየቅ አለብዎ - ይህ ጊዜ ከ 10 የካላንደር ቀናት ያጠረ ሊሆን ይችላል።
- እርስዎ በቅሬታ እና የይግባኝ ሂደት ወቅት ከAmerigroup DC አንድ ሰው እርዳታ የማግኘት መብት አለዎት።
- እራስዎን የመወከል ወይም በቤተሰብ ተንከባካቢ፣ ጠበቃ፣ ወይም ሌላ ወኪል የመወከል መብት አለዎት።
- ለማንኛውም ልዩ የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች መቆያ እንዲመቻችልዎ የመጠየቅ መብት አለዎት።
- እርስዎ በቂ የTTY/TTD ችሎታዎች እና ማየት ለተሳናቸው አገልግሎቶች የማግኘት መብት አሎት።
- እርስዎ በቂ የትርጉም እና የአስተርጓሚ አገልግሎቶች የማግኘት መብት አለዎት።
- እርስዎ ከቅሬታዎ፣ ይግባኝዎ፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቱ ጋር የተያያዙ ሁሉንም ሰነዶች የማየት መብት አለዎት።

ስለ ቅሬታዎቹ እና ይግባኞቹ/ፍትሃዊ ችሎት ሂደት ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር ይደውሉ በ800-600-4441 (TTY 711)።

**<u>የግላዊነት ልምድ ማስታወቂያ</u>**

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የሚመለከት የሕክምና መረጃ አገልግሎት ላይ እንዴት ሊውል እንደሚችል እና ይፋ እንደሚሆን እና ይህን መረጃ እርስዎ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። እባክዎ በጥንቃቄ ያንብቡት።

ስለ ጤናዎ እና ስለ ገንዘብዎ ያለው መረጃ ሚስጥራዊ ነው። ሕጉ ደህንነቱ የሚጠበቅ የጤና መረጃ (PHI) በመባል የሚጠራውን ይህን ዓይነት መረጃን፣ ለአባሎቻችን ደህነነቱ በጠበቀ መልኩ እንድንጠብቅ ያስገድደናል። ያ ማለት እርስዎ አሁን አባል ከሆኑ ወይም ከዚህ በፊት አባል ከነበሩ፣ የመረጃዎ ደህንነት የተጠበቀ ነው ማለት ነው።

ለጤና እቅዳችን ብቁ ሆነው ከተመዘገቡ በኋላ፣ ለMedicaid እና የህጻናት የጤና መድን ፕሮግራም ከስቴት ኤጀንሲዎች

ስለእርስዎ መረጃ እናገኛለን። በተጨማሪም ለጤና እንክብካቤዎ እንድንፈቅድ እና ክፍያ እንድንፈጽም፣ ከእርስዎ ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሆስፒታሎች መረጃ እናገኛለን።

የፌደራል ህግ በጽሁፍ የተነገረንን፣ ወይም በኮምፒዩተር የተቀመጠንPHI ለመጠበቅ ማድረግ ስለሚገባን ነገሮች ለእርስዎ መንገር እንዳለብን ያስገድደናል። በተጨማሪ እኛ ደህንነቱን እንዴት እንደምንጠብቅ ልንነግርዎ ይገባል።PHIን ለመጠበቅ፥

- በወረቀት ላይ (ቁሳዊ ተብሎ የሚጠራ)፣ እኛ፥
  - ቢሮዎቻችንን እና ፋይሎቻችንን እንቆልፋለን
  - ሌሎች እንዳያገኙት የጤና መረጃ የያዙ መረጃዎችን እናስወግዳለን
- በኮምፒውተር ላይ የተቀመጠ (ቴክኒካል ተብሎ የሚጠራው)፣ እኛ፥
  - ትክክለኛዎቹ ሰዎች ብቻ እንዲገቡ የይለፍ ቃሎችን እንጠቀማለን
  - ሲስተሞቻችንን ለመከታተል ልዩ ፕሮግራሞችን እንጠቀማለን
- ለእኛ፣ ለሐኪሞች ወይም ለዲስትሪክት የሚሰሩ ሰዎች የሚጠቀሙት ወይም የሚያጋሩት፣ እኛ፥
  - የመረጃ ደህንነትን ለመጠበቅ መመሪያዎችን እናወጣለን (ፖሊሲዎች እና ሥነ ሥርዓቶች ተብለው ይጠራሉ)
  - ለእኛ የሚሰሩ ሰዎች መመሪያዎቹን እንዲከተሉ እናስተምራቸዋለን

**እኛ የእርስዎንPHI መጠቀም እና ማጋራት የምንችለው መቼ ነው?**

የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን የእርስዎንPHI ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎ እርስዎ ለመረጡት ሰው ልናጋራ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ፣ **ያለእርስዎ** ይሁንታ ልንጠቀምበት እና ልናጋራው እንችላለን፥

- **ለህክምና እንክብካቤዎ (ህክምና)**
  - ሐኪሞች፣ ሆስፒታሎች እና ሌሎች እርስዎ የሚያስፈልግዎትን እንክብካቤ እንዲሰጡ ለመርዳት
- **ለክፍያ ምክንያቶች**
  - ለእርስዎ እንክብካቤ ክፍያ ከሚጠይቁን ሐኪሞች፣ ክሊኒኮች እና ሌሎች ጋር መረጃ ለመጋራት።
  - የጤና እንክብካቤ ወይም አገልግሎቶችን ከማግኘትዎ በፊት እንደምንከፍልልዎ ከተናገርን
  - እርስዎን ለመደገፍ እና ያሉትን ጥቅማጥቅሞች እንዲያገኙ ለማገዝ
- **ለጤና አጠባበቅ ጉዳይ ምክንያቶች (ሥራዎች)**
  - የኦዲት፣ ማጭበርበር እና አላግባብ መጠቀምን የመከላከል ፕሮግራሞችን፣ እቅድ ማውጣትን እና የዕለት ተዕለት ሥራን ለመርዳት
  - ፕሮግራሞቻችንን የተሻሉ ለማድረግ የሚያስችሉ መንገዶችን ለማግኘት

  የእርስዎንPHI ለጤና መረጃ ልውውጦች ለክፍያ፣ ለጤና እንክብካቤ ስራዎች እና ለህክምና ልንሰጥ እንችላለን። ይህንን የማይፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎን ለበለጠ መረጃ **myamerigroup.com/DC** ይጎብኙ።
- **ለሕዝብ ጤና ምክንያቶች**
  - የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ሰዎችን ከመታመም ወይም ከመጎዳት እንዲጠብቁ ለመርዳት
- **ለእንክብካቤዎ እገዛ ለሚያደርጉ ወይም ለሚከፍሉ ሌሎች ሰዎች ጋር**
  - የእርስዎ ይሁንታዎን ከነገሩን ለቤተሰብዎ ወይም የጤና እንክብካቤዎ ላይ እገዛ ለሚያደርግልዎ ወይም ለሚከፍልልዎ እርስዎ ለመረጡት ሰው
  - ስለራስዎ መናገር የማይችሉ ከሆነ እና ለእርስዎ የተሻለ ከሆነ፣ ለጤና እንክብካቤዎ እገዛ ከሚያደርግልዎ ወይም ከሚከፍልልዎ ሰው ጋር

ለሕክምናዎ፣ ክፍያ፣ የእለት ተለት ሥራ፣ የምርምር ጥናት ወይም ከታች ለተዘረዘሩት ሌሎች ነገሮች ውጪ የእርስዎንPHI ከመጠቀማችን ወይም ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን ይሁንታ በጽሁፍ ማግኘት አለብን። ስለ እርስዎ ከሐኪምዎ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን ከማጋራታችን በፊት የእርስዎን የጽሁፍ ይሁንታ ማግኘት አለብን። በተጨማሪ የእርስዎንPHI እኛ የምንሸጥ ከሆነ ወይም ለገበያ የምንጠቀምበት ወይም የምናጋራው ከሆነ የእርስዎ የጽሁፍ ይሁንታ ያስፈልገናል።

በጽሁፍ የሰጡትን ይሁንታን መተው እንደሚፈልጉ በጽሁፍ ሊነግሩን ይችላሉ። እኛ መመለስ አንችልም የእርስዎ ይሁንታ ባለበት ወቅት የተጠቀምነውን ወይም ያጋራነውን። ነገር ግን ወደፊት የእርስዎንPHI መጠቀም ወይም ማጋራት እናቆማለን።

**ሌሎች መንገዶች - ወይም ህጉ የሚፈቅድልን - የእርስዎንPHI እንድንጠቀም፥**

- ፖሊስን እና ሌሎች ህግ የሚያስከብሩ ሰዎችን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ አላግባብ መጠቀምን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግPHI ን ልንጠቀም እንችላለን።
- ስንጠየቅ ፍርድ ቤቱን ለመርዳት። ለምሳሌ፣ በፍርድ ቤት የሚያያዙ እንደ አቤቱታ ወይም የፍርድ ቤት መጥሪያ የመሳሰሉ ህጋዊ ሰነዶች ላይ ምላሽ ለመስጠትPHI ልንጠቀም እንችላለን።
- ለጤና ቁጥጥር ኤጀንሲዎች ወይም ለሌሎች ለመንግስት አንዳንድ ስራዎችን ለሚሰሩ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ ለኦዲት ወይም ለፈተና መረጃ እንሰጣለን።
- የእርስዎን ስም እና የሞት መንስኤ ለማወቅ እንዲረዳቸው ለሬሳ ምርመራ ሐኪሞች፣ የህክምና መርማሪዎች ወይም የቀብር አስፈጻሚዎች።
- የሰውነት ክፍሎችዎን ለሳይንስ ወይም ለጥናት ምርምር ለመስጠት ሲጠይቁ ለመርዳት። ለምሳሌ፣ ሲሞቱ የሰውነት ክፍልዎን ለመለገስ ከተስማሙ መረጃዎን ልናጋራ እንችላለን።
- እርስዎን ወይም ሌሎች ከመታመም ወይም ክፉኛ ከመጎዳት ለመጠበቅ። ለምሳሌ፣ እርስዎ ወይም ሌሎች በአስቸኳይ ሁኔታ ውስጥ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ለመከላከል የእርስዎን PHI ልናጋራ እንችላለን።
- ለሠራተኞች ካሳ መረጃ ለመስጠት። ለምሳሌ፣ በስራ ላይ ሆነው ከታመሙ ወይም ከተጎዱ የእርስዎን መረጃ ልናጋራ እንችላለን።

**መብቶችዎ ምንድን ናቸው?**

- የእርስዎንPHI ለማየት እና ቅጂውን ለማግኘት መጠየቅ ይችላሉ። ነገር ግን መሉ የሕክምና መረጃዎ የለንም። ሙሉ የህክምና መረጃዎን ቅጂ ከፈለጉ፣ ሐኪምዎን ወይም የጤና ክሊኒክዎን ይጠይቁ።
- የሆነ ችግር አለ ወይም የጎደለ ነገር አለ ብለው ካሰቡ ያለንን የእርስዎን የሕክምና መረጃ እንድንቀይረው እኛን መጠየቅ ይችላሉ።
- አንዳንድ ጊዜ፣ የእርስዎንPHI እንዳናጋራ ሊጠይቁን ይችላሉ። ነገር ግን በጥያቄዎ የግድ መስማማት የለብንም ። ለምሳሌ፣ PHI የክሊኒካል ማስታወሻዎች አካል ከሆነ እና በህግ ሊለቀቅ የማይችል ከሆነ ጥያቄዎ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።
- ካለን የእርስዎ አድራሻ ውጪ ወዳለ አድራሻ ወይም በተወሰነ ሌላ መንገድPHI እንድንልክልዎ እኛን መጠየቅ ይችላሉ። ባለን የእርስዎ አድራሻ መላክ እርስዎን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ ይህን ማድረግ እንችላለን።
- ባለፉት ስድስት ዓመታት የእርስዎንPHI ለሌላ ሰው ያጋራንበትን ሁሉንም መረጃ እንድንነግርዎ ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህ ለጤና እንክብካቤ፣ ለክፍያ፣ ለዕለትተዕለት የጤና እንክብካቤ ሥራ ወይም እዚህ ባልዘረዘርናቸው ሌሎች ምክንያቶች ያጋራንበትን ጊዜ አይዘረዝርም።
- የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በኢሜይል እንዲላክልዎ የጠየቁ ቢሆንም እንኳን የወረቀት ቅጂ እንዲላክልዎ በማንኛውም ጊዜ መጠየቅ ይችላሉ።
- ለአንድ አገልግሎት ሙሉዉን ክፍያ ከከፈሉ፣ ስለዚያ አገልግሎት መረጃውን ለእኛ እንዳያጋሩ ሐኪምዎን መጠየቅ ይችላሉ።

**እኛ ምን ማድረግ አለብን?**

- ህጉ በዚህ ማስታወቂያ ከገለጽነው ውጪ የእርስዎንPHI ሚስጥራዊ ማድረግ እንዳለብን ያስገድዳል።
- ህጉ ስለ ሚስጥራዊነት እንድናደርግ የሚያስገድደን ምን እንደሆነ ለእርስዎ መንገር አለብን።
- በዚህ ማስታወቂያ እናደርጋለን ብለን የገለጽናቸውን ነገሮች ማድረግ አለብን።
- እርስዎ ከጠየቁ እና አደጋ ላይ ከሆኑ፣ የእርስዎን PHI ወደ ሌላ አድራሻ ወይም መደበኛ ከሆነው ፖስታ ውጪ በሌላ መንገድ መላክ አለብን።

- እንዳናጋራው ከነገሩን በኋላ የእርስዎንPHI ማጋራት ካለብን ለእርስዎ መንገር አለብን።
- እኛ እዚህ እናደርጋቸዋለን ብለን ከገለጽናቸው በላይ የስቴት ህጎች ማድረግ እንዳለብን የሚያስገድዱ ከሆነ፣ እነዚያን ህጎች እንከተላለን።
- የእርስዎPHI እንደተጣሰ ካሰብን እኛ ለእርስዎ ማሳወቅ አለብን።

**እኛ ልናገኝዎ እንችላለን**
እኛ፣ ተባባሪዎቻችን እና/ወይም አቅራቢዎቻችንን ጨምሮ፣ አውቶማቲክ የስልክ መደወያ ስርዓት እና/ወይም ቀድሞ የተቀዳ መልእክትን በመጠቀም፣ ገመድ አልባ የስልክ ቁጥርን ጨምሮ ወደሚሰጡን ማንኛውም የስልክ ቁጥሮች ላይ እንድንደውል ወይም የጽሁፍ መልእክት እንድንልክ ተስማምተዋል። እነዚህ የስልክ ጥሪዎች ወይም የጽሁፍ መልእክቶች ስለህክምና አማራጮች፣ ሌሎች ከጤና ጋር የተያያዙ ጥቅማጥቅሞች እና አገልግሎቶች፣ ምዝገባ፣ ክፍያ፣ ወይም የክፍያ መጠየቂያ ሊሆኑ የሚችሉ ስሊሆን ነገር ግን በዚህ የተገደቡ አይደሉም።

**ጥያቄዎች ካሉዎትስ?**
ስለ የኛ የሚስጥራዊነት መመሪያችን ጥያቄዎች ካሎት ወይም መብቶችዎን መጠቀም ከፈለጉ፣ እባክዎ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር በ800-600-4441 ይደውሉ። መስማት የተሳነዎት ከሆኑ ወይም የመስማት ችግር ካለብዎት፣ በTTY 711 ይደውሉ።

**ቅሬታ ካለዎትስ?**
እኛ እዚህ ያለነው ለማገዝ ነው። የእርስዎ PHI ደህንነቱ እንዳልተጠበቀ ከተሰማዎ፣ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ወይም የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች ዲፓርትመንትን ማግኘት ይችላሉ።

**ለጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ይጻፉ ወይም ይደውሉ፥**

Office for Civil Rights
U.S. Department of Health and Human Services
200 Independence Ave. SW
Washington, DC 20201
ስልክ፥ 1-800-368-1019
TDD፥ 1-800-537-7697

ይህን የጤና መድን ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ህግ (HIPAA) ማስታወቂያ እና የእርስዎንPHI ደህንነት የምንጠብቅባቸውን መንገዶች የመቀየር መብታችን የተጠበቀ ነው። እንዲያ ከሆነ፣ እኛ ስለለውጦቹ በመጽሄቶች እንነግርዎታለን። በተጨማሪም በድረገጽ በ amerigroup.com/privacy-policy ላይ እንለጥፋቸዋለን።

**ዘር፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ እና የፆታ ማንነት**

ስለ እርስዎ ዘር፣ ብሄር፣ ቋንቋ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ እና የፆታ ማንነት መረጃ ልንቀበል እንችላለን። ይህን መረጃ በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተገለጸው እንጠብቀዋለን።

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት እንጠቀማለን፥
- የሚያስፈልግዎትን መረጃ ማግኘትዎን ለማረጋገጥ
- የጤና ውጤቶችን የሚያሻሽሉ ፕሮግራሞችን ለመፍጠር
- የጤና ትምህርት መረጃ ለማዘጋጀት እና ለመላክ
- ስለ ቋንቋ ፍላጎቶችዎ ለሐኪሞች ለማሳወቅ
- የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ለመስጠት

ይህንን መረጃ ለሚከተሉት <u>**አንጠቀምበትም**</u>፥
- የጤና መድን ለመስጠት
- ለአገልግሎቶች ምን ያክል ለማስከፈል ለመወሰን
- ጥቅማጥቅሞችን ለመወሰን
- ላልተፈቀደላቸው ተጠቃሚዎች ለመግለጽ

**የግል መረጃዎ**

የስቴት ህጎች የHIPAA የግላዊነት መመሪያ ላይ ካለው በላይ ግዴታ የሚጥሉብን ከሆነ ያንን እናከብራለን። በዚህ ማስታወቂያ ላይ እንደተናገርነው የግል መረጃን (PI) ልንጠይቅ፣ ልንጠቀም እና ልናጋራ እንችላለን። የእርስዎPI ለህዝብ ይፋ አይደለም እና እርስዎ ማን እንደሆኑ ይነግረናል። አብዛኛውን ጊዜ የሚወሰደው ለመድን ዓላማ ነው።

- የእርስዎንPI ስለእርስዎ የሚከተሉትን ውሳኔዎች ለመወሰን ልንጠቀም እንችላለን፥
  - ጤና
  - ልማዶች
  - የትርፍ ጊዜ ማሳለፊያዎች
- ስለ እርስዎPI ከሌሎች ሰዎች ወይም ቡድኖች ልናገኝ እንችላለን ለምሳሌ፥
  - ሐኪሞች
  - ሆስፒታሎች
  - ሌሎች የመድን ኩባንያዎች
- በአንዳንድ ሁኔታዎች የእርስዎን ይሁንታ ሳናገኝ ከኩባንያችን ውጪ ላሉ ሰዎች ወይም ቡድኖችPI ልናጋራ እንችላለን። ለምሳሌ፣ ስራችንን ለማስኬድ እንዲረዱን ከምንቀጥራቸው የይገባኛል ጥያቄዎች እና የሂሳብ አከፋፈል አቅራቢዎች ጋርPI ልናጋራ እንችላለን።
- ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችን በፊት የመከልከል እድል ለእርስዎ ለመስጠት እናሳውቅዎታለን።
- የእርስዎንPI እንድንጠቀም ወይም እንድናጋራ ካልፈለጉ ለኛ እንዴት እንደሚያሳውቁን እንነግርዎታለን።
- የእርስዎንPI የማየት እና የመቀየር መብት አሎት።
- የእርስዎPI ደህንነቱ የተጠበቀ መሆኑን እናረጋግጣለን።

<u>**የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ**</u>

የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ፕሮግራም ከእርስዎMCP የጤና እንክብካቤ እንዲያገኙ እርስዎን የሚያግዝ የColumbia ዲስትሪክት መንግስት ፕሮግራም ነው። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፥

- ማግኘት የሚገባዎን የጤና እንክብካቤ መብት ማብራራት፤
- የጤና እንክብካቤዎን የሚመለከቱ ጥያቄዎችዎን እና ስጋቶችዎ ላይ ምላሽ መስጠት፤
- የMCP ተመዝጋቢ በመሆንዎ ያሎትን መብቶች እና ግዴታዎችን እንዲረዱ ማገዝ፤
- የሚያስፈልግዎትን አስፈላጊ የሕክምና አገልግሎቶች እንዲያገኙ መርዳት።
- የጤና እንክብካቤዎ ጥራትን በሚመለከት ሊኖርዎ የሚችሉ ጥያቄዎችን እና ስጋቶችን መመለስ።
- ከሐኪምዎ ጋር ወይም ሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ያለብዎትን ችግሮች እንዲፈቱ ማገዝ።
- ከMCP ጋር ያሉ አቤቱታዎችን እና ችግሮችን ለመፍታት እርስዎን መረዳት።
- የይግባኝ ሂደቶች ላይ ማገዝ፤ እና
- የፍትሃዊ ችሎት ጥያቄ ማቅረብ ላይ እርስዎን መርዳት።

የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂን ለማግኘት፣ እባክዎ ይደውሉ202-724-7491 ወይም877-685-6391 (ከክፍያ ነጻ)። የጤና እንክብካቤ እንባ ጠባቂ ቅሬታዎች፣ ይግባኞች፣ ወይም ፍትሃዊ ችሎቶች ላይ ውሳኔ አይሰጥም። የጤና እንክብካቤ የእንባ ጠባቂ እና የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ የሚገኘው በ፥


One Judiciary Square
441 4th Street, NW
Suite 250 North
Washington, DC 20001
ስልክ፥ 202-724-7491
ፋክስ፥ 202-442-6724
ከክፍያ ነጻ ቁጥር፥ 877-685-6391
ኢሜይል፥ healthcareombudsman@dc.gov

**ትርጉሞች**

| | |
|---|---|
| **የቀደመ መመሪያ** | እርስዎ ከታመሙ ወይም ከተጎዱ እና ስለራስዎ መናገር ባይችሉ ሌሎች ስለሚፈልጉት እና የማይፈልጉት የጤና እንክብካቤ እንዲያዉቁ የሚያደርግ፣ በጽሁፍ የሆነ፣ እርስዎ የፈረሙት ህጋዊ ወረቀት ነው። |
| **ጠበቃ** | እርስዎ የሚፈልጉትን የጤና እንክብካቤ እና ሌሎች አገልግሎቶችን እንዲያገኙ የሚያግዝዎ ሰው። |
| **ይግባኝ** | ይግባኝ ማለት Amerigroup DC የጤና ሕክምና አገልግሎቶችን ወይም ላገኟቸው አገልግሎቶች ክፍያ በመከልከል በሚሰጠው አንድ ውሳኔ ሳይስማሙ ሲቀር የሚያቀርቡት ልዩ አቤቱታ ነው። በተጨማሪ በውሳኔው ካልተስማሙ እያገኙ ያሉትን አገልግሎቶች ለማስቀም ይህን ዓይነት ልዩ አቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። |
| **ቀጠሮ** | የእርስዎን የጤና እንክብካቤ ፍላጎቶች ለማሟላት እርስዎ እና ሐኪምዎ ጊዜ እና ቀን መድቡ። |
| **የባህሪይ ጤና** | የአእምሮ ጤና ሁኔታዎች (የአእምሮ ሕመሞችን እና የስሜት መቃወስን ጨምሮ) እና የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መዛባት (ሱስ እና ኬሚካላዊ ጥገኝነት መታወክን የሚያካትቱ) ጃንጥላ ቃል። ቃሉ እንዲሁ አብሮ የሚመጡ የአእምሮ ጤና ሁኔታዎችን እና የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም መዛባትን (SUDS) መከላከል እና ማከምን ያመለክታል። |
| **የሕክምና አስተዳዳሪ** | የሚያስፈልግዎትን ሕክምና፣ ድጋፍ፣ እና ጤናማ ሆነው ለመቆየት የሚያስፈልግዎትን መረጃ እንዲያገኙ እርስዎን ለመርዳት ከAmerigroup DC ጋር የሚሰራ ሰው ነው። |
| **ምርመራ** | *የማጣሪያ ምርመራን ይመልከቱ* |
| **የወሊድ መቆጣጠሪያ** | የወሊድ መቆጣጠሪያ ጋር የተያያዙ አቅርቦቶች |
| **ሽፋን ያላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለሚሰጡ የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች በAmerigroup DC ክፍያ የሚከፈልባቸው። |
| **መርዛማ ነገር ከሰውነት ውስጥ ማስወጣት** | እንደ አደንዛዥ እጽ እና የአልኮል መጠጥ የመሳሰሉ ጎጂ ነገሮችን ከሰውነት ማስወገድ። |
| **የበሽታ መቆጣጠር ፕሮግራም** | ከባድ በሽታ ያለባቸው ወይም እንደ አስም፣ ከፍተኛ የደም ግፊት፣ ወይም የአእምሮ በሽታ የመሳሰሉ ልዩ የጤና ሕክምና የሚፈልጉ ሰዎች የሚያስፈልጋቸውን እንክብካቤ እና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የሚረዳ ፕሮግራም። |
| **ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የሕክምና መሳሪያ (DME)** | ቤትዎ ውስጥ እንዲጠቀሙት ሐኪምዎ የሚጠይቅዎ ወይም የሚያዝዎ ልዩ የሕክምና መሳሪያ። |
| **የድንገተኛ ሁኔታ ሕክምና** | ለከባድ፣ ድንገተኛ፣ አንዳንድ ጊዜ ለህይወት አስጊ ለሆነ ሁኔታ ወዲያውኑ የሚያስፈልግዎ ሕክምና። |
| **ተመዝጋቢ** | በAmerigroup DC መረብ ውስጥ ባለ አቅራቢ አማካኝነት የጤና ሕክምና የሚያገኝ ሰው። |
| **የተመዝጋቢ መታወቂያ (ID) ካርድ** | እርስዎ የAmerigroup DC ተመዝጋቢ መሆንዎን ሐኪሞችዎ፣ ሆስፒታሎች፣ መድሃኒት ቤቶች፣ እና ሌሎች እንዲያውቁት የሚያደርግ ካርድ። |
| **ፍትሃዊ ችሎት** | ይግባኝዎ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማሙ የDC የአስተዳደር ችሎት ቢሮ ጋር ፍትሃዊ ችሎት መጠየቅ ይችላሉ። |
| **የቤተሰብ ምጣኔ** | አገልግሎቶቹ የእርግዝና ምርመራዎች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ፣ በግብረስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ምርመራ እና ሕክምና፣ እና የHIV/AIDS ምርመራ እና የምክር አገልግሎትን ያካትታል። |
| **የቤተሰብ እና አጠቃላይ ሕክምና ሐኪም** | መላውን ቤተሰብ ሊያክም የሚችል ሐኪም። |
| **ቅሬታ** | በሚያገኙት ሕክምና፣ ወይም Amerigroup DC በሚሰጠው የጤና ሕክምና አገልግሎቶች ደስተኛ ካልሆኑ፣ ቅሬታ ለማቅረብ የተመዝጋቢ አገልግሎቶች ጋር መደወል ይችላሉ። |

| | |
|---|---|
| **የመመሪያ መጽሃፍ** | ይህ መጽሀፍ ስለ Amerigroup DC እና ስለኛ አገልግሎቶች መረጃ ይሰጥዎታል። |
| **መስማት የተሳነው** | በሚገባ መስማት የማይችሉ ከሆነ ወይም መስማት የተሳኖት ከሆኑ |
| **ክትባት** | መርፌ ወይም ክትባት። |
| **የውስጥ ደዌ ሕክምና ሐኪም** | የአዋቂዎች እና እድሜያቸው ከ 14 ዓመት በላይ የሆኑ ልጆች ሐኪም። |
| **የአስተርጓሚ/የትርጉም አገልግሎቶች** | የራስዎን ቋንቋ ከሚናገር ሰው ጋር ለማውራት ወይም ከሐኪምዎ ጋር ወይም ከሆስፒታሉ ጋር ለማውራት ከAmerigroup DC የሚያገኙት እርዳታ። |
| **የሚተዳደር እንክብካቤ ድርጅት (MCP)** | እርስዎ የሚያስፈልግዎትን የጤና ሕክምና እና የጤና አገልግሎቶች እንዲያገኙ የColumbia ዲስትሪክት የሚከፍለው ኩባንያ። |
| **የወሊድ ጊዜ** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና የምትቆይበት እና ከወሊድ በኋላ ያለው አጭር ጊዜ። |
| **የአእምሮ ጤና** | አንድ ሰው በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የሚያስበው፣ የሚሰማው፣ እና የሚያደርገው ድርጊት። |
| **የመረብ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ እና የAmerigroup DC አካል የሆኑ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሽፋን የሌላቸው አገልግሎቶች** | በአቅራቢ ለተሰጠ የጤና ሕክምና Amerigroup DC ክፍያ የማይፈጽምበት። |
| **አዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም (OB/GYN)** | አዋላጅ ሐኪም/የጽንስ ሐኪም፤ እርግዝናን ጨምሮ፣ የሴት ጤናን ለማከም የሰለጠነ ሐኪም። |
| **ከአውታረ-መረብ ውጭ አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ እና የAmerigroup DC አካል ያልሆኑ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **መድሃኒት ቤት** | መድሃኒትዎን የሚመርጡበት ቦታ። |
| **የሐኪም የጥቅማጥቅም እቅድ** | ሐኪምዎ ከAmerigroup DC ጋር ማንኛውም ልዩ ትብብር ካላቸው ይነግርዎታል። |
| **የድህረ ወሊድ ሕክምና** | ልጅዋን ከወለደች በኋላ አንዲት ሴት የምታገኘው የጤና ሕክምና ነው። |
| **የቅድመ ወሊድ ሕክምና** | አንዲት ሴት ነፍሰጡር ሆና በምትቆይበት ጊዜ ሁሉ የሚሰጥ የሕክምና እንክብካቤ ነው። |
| **የመድሃኒት ማዘዣ** | ዶክተርዎ የሚያዙልዎት መድሃኒት። የማዘዣ መድሃኒቱን ለመምረጥ ወደ ፋርማሲው መውሰድ አለብዎት። |
| **የመከላከል የምክር አገልግሎት** | ጤናማ ሆነው ለመቆየት ወይም ከመታመም ወይም ከመጎዳት እራስዎን ለመከላከል ስለሚያስችሉ ዘዴዎች ከአንድ ሰው ጋር ማውራት ሲፈልጉ። |
| **ዋና የህክምና አቅራቢ (PCP)** | አብዛኛውን ጊዜ ለእርስዎ ሕክምና የሚሰጡት ሐኪም። |
| **የቀደመ ፈቃድ** | የጤና እንክብካቤ ወይም ሕክምና ለማግኘት ከAmerigroup DC የሚያገኙት የጽሁፍ ፈቃድ። |
| **የአቅራቢ ማውጫ** | የAmerigroup DC አካል የሆኑ የሁሉም አቅራቢዎች ዝርዝር። |
| **አቅራቢዎች** | ጤናዎን የሚንከባከቡ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ የጥርስ ሐኪሞች፣ እና ሌሎች ሰዎች። |
| **ሪፈራል** | በሌላ ሐኪም እንዲታዩ እርስዎን ለመላክ ዋና ሐኪምዎ የሚሰጠው የጽሁፍ ማስታወሻ። |
| **መደበኛ ህክምና** | ከዋና የሕክምና አቅራቢዎ ወይም ዋና የሕክምና አቅራቢዎ ከላከዎ ሐኪም የሚያገኙት መደበኛ ሕክምና። መደበኛ የሕክምና ምርመራ፣ የአካል ምርመራ፣ የጤና ማጣሪያ ምርመራ፣ እና እንደ የስኳር በሽታ፣ አስም፣ እና የደም ግፊት የመሳሰሉ የጤና ችግሮችን በተመለከተ የሚያገኙት መደበኛ ሕክምናን ያካትታል። |
| **የማጣሪያ ምርመራ** | እርስዎ ጤናማ መሆንዎን ለማወቅ ሐኪምዎ ወይም ሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ ሊያከናውኑት የሚችሉ ምርመራ። |
| **የራስ-የሪፈራል አገልግሎቶች** | ከዋና ሐኪምዎ የጽሁፍ ማስታወሻ ወይም ሪፈራል ሳያስፈልግዎ ሊያገኟቸው የሚችሉ የተወሰኑ አገልግሎቶች። |
| **አገልግሎቶች** | ከሐኪምዎ ወይም ከሌላ የጤና ሕክምና አቅራቢ የሚያገኙት ሕክምና። |
| **ልዩ የጤና ሕክምና ፍላጎቶች** | ሌሎች አዋቂዎች ከሚያስፈልጋቸው በላይ ወይም የተለየ የጤና ሕክምና እና ሌሎች ልዩ አገልግሎቶች የሚፈልጉ አዋቂዎች። |

| | |
|---|---|
| **ስፔሺያሊስት** | ልዩ ሕክምና ለመስጠት የሰለጠነ ሐኪም፥ እንደ የጆሮ፣ የአፍንጫ፣ የጉሮሮ፣ ወይም የእግር ሐኪም። |
| **የስፔሺያሊቲ ሕክምና** | የጤና ሕክምናው የሚሰጠው ልዩ ዓይነት የጤና ሕክምና ለመስጠት በሰለጠኑ ሐኪሞች ወይም ነርሶች ነው። |
| **የማምከን ሕክምናዎች** | ልጅ መውለድ ወደፊት ሳይፈልጉ ሲቀር ሊያደርጉት የሚችሉት የቀዶ ጥገና። |
| **የንጥረ ነገር አላግባብ መጠቀም መታወኮች (ሳብስታንስ አብዉስ ዲስኦርዴርስ (SUD))** | በአልኮል ወይም በአደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀም የሚሰቃይ በሽተኛ አያያዝ እና እንክብካቤ፣ ይህ በመጠቀም የተከሰተ እንደሆነ የሚታወቅ። |
| **የትራንስፖርት አገልግሎቶች** | ወደ ቀጠሮ ቦታዎ ለመሄድ ከAmerigroup እርዳታ። የሚያገኙት የትራንስፖርት ዓይነት የሚወሰነው በሚያስፈልግዎ የሕክምና ዓይነት ነው። |
| **ሕክምና** | ከሐኪምዎ የሚያገኙት ሕክምና። |
| **አስቸኳይ ህክምና** | ወዲያውኑ ሳይሆን፣ በ 24 ሰዓታት ውስጥ ማግኘት ያለብዎ ሕክምና። |
| **ማየት የተሳነው** | በሚገባ ማየት የማይችሉ ከሆነ ወይም ማየት የተሳኖት ከሆነ። |

## Amerigroup District of Columbia, Inc.

በቀን 24 ሰዓት፣ በሳምንት 7 ቀናት ሊደውሉልን፣ ወይም ቢሯችን ከሰኞ እስከ አርብ ከጧት 8፡00 እስከ ምሽት 6፡00 መምጣት ይችላሉ። እንዴት እንደሚያገኙን አቅጣጫውን ለማወቅ፣ ይደውሉ በ 800-600-4441 (TTY 711) (ከክፍያ ነፃ)።


609 H Street NE
Ste. 200
Washington, DC 20002

የቢሮ የስራ ሰዓታት፡- ከጧት 8:00 እስከ ምሽት 6:00

202-548-6700
800-600-4441 (TTY 711)

Amerigroup

District of Columbia

የተመዝጋቢ አገልግሎቶች፥

609 H St. NE
Suite 200
Washington, DC 20002

**202-548-6700**

**800-600-4441 (TTY 711)** (ከክፍያ ነፃ)

**myamerigroup.com/DC**

DHCF Department of Health Care Finance

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

This program is brought to you by the Government of the District of Columbia Department of Health Care Finance.